የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአምስተኛ ዓመት ቁጥር ፷፪
አዲስ አበባ ጳጉሜ ፬ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

15th Year No. 62
ADDIS ABABA 9th September, 2009

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፮፻፶፫/፪ሺ፩ ዓ.ም

ከኃላፊነት የተነሱ የሀገርና የመንግሥት መሪዎች፣ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎች፣ የምክር ቤት አባላትና ዳኞች መብቶችና ጥቅሞች አዋጅ… ገጽ ፬ሺ፱፻፴፩

CONTENTS

**Proclamation No. 653/2009**

Rights and Benefits of Outgoing Heads of State and Government, Senior Government Officials, Members of Parliament and Judges Proclamation …..Page 4931

## አዋጅ ቁጥር ፮፻፶፫/፪ሺ፩

## ከኃላፊነት የተነሱ የሀገርና የመንግሥት መሪዎች፣ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎች፣የምክር ቤት አባላትና ዳኞች የሚያገኙዋቸውን መብቶችና ጥቅሞች ለመወሰን የወጣ አዋጅ

የሀገርና የመንግሥት መሪዎች፣ ከፍተኛ የመን ግሥት ኃላፊዎች፣ የምክር ቤት አባላትና ዳኞች ሕዝባዊ አደራ በመሸከም ለሀገርና ለሕዝብ ጥቅም የሚሠሩ በመሆናቸው ከኃላፊነት ሲነሱ ከጉስቁልና የራቀ ኑሮ እንዲኖሩ ማድረግና ለጥቃት ተጋላጭ እንዳይሆኑ ጥበቃና ከለላ መስጠት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የሀገርና የመንግሥት መሪዎች፣ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎች፣ የምክር ቤት አባላትና ዳኞች በኃላፊነት በነበሩበት ወቅት ያካበቱትን ዕውቀትና ልምድ ለመጠቀም አመቺ ሁኔታ መፍጠር ስለሚያስ ፈልግ፤

ሥራ ላይ ያሉ የሀገርና የመንግሥት መሪዎች፣ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎች፣ የምክር ቤት አባላትና ዳኞች ለወደፊት ኑሯቸው ሳይሰጉ ለአገር ልማ ትና እድገት በቅንነት፣ በታማኝነትና በትጋት እንዲ ሰሩ ማበረታታ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭/፩/ መሠረት የሚከተ ለው ታውጇል።

## PROCLAMATION NO. 653/2009

## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE RIGHTS AND BENEFITS OF OUTGOING HEADS OF STATE AND GOVERNMENT, SENIOR GOVERNMENT OFFICIALS, MEMBERSOF PARLIAMENT AND JUDGES

**WHEREAS,** it is necessary that outgoing Heads of State and Government, Senior Government Officials, Members of Parliament and Judges shall be guaranteed a life that is free of depressing conditions and need to be protected from victimization in consideration of the services they provided to the nation and the public by shouldering huge public trust during their terms in office;

**WHEREAS,** it is necessary to create enabling conditions to take advantage of the knowledge and experience of outgoing Heads of State and Government, Senior Government Officials, Members of Parliament and Judges accumulated through their terms in office;

**WHEREAS,** serving Heads of State and Government, Senior Government Officials, Members of Parliament and Judges need to be encouraged to positively and faithfully exert their utmost effort for the development and progress of the country, without worrying about their future;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## ክፍል አንድ
## ጠ ቅ ላ ላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ከኃላፊነት የተነሱ የሀገርና የመንግሥት መሪዎች፣ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎች፣ የምክር ቤት አባላትና ዳኞች መብቶችና ጥቅሞች አዋጅ ቁጥር ፮፻፶፫/፪ሺ፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም ካላሰጠው በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ "የሀገር መሪ" ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት ነው፤

፪/ "የመንግሥት መሪ" ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር ሲሆን ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርን ይጨምራል፤

፫/ "ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊ" ማለት ሚኒስትር፣ ሚኒስትር ዴኤታ ወይም ምክትል ሚኒስትር ነው፤

፬/ "ሚኒስትር" ማለት ማንኛውም ሚኒስትር ሲሆን በሚኒስትር ደረጃ ያለ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊንም ይጨምራል፤

፭/ "ሚኒስትር ዴኤታ" ማለት ማንኛውም ሚኒስትር ዴኤታ ሲሆን በሚኒስትር ዴኤታ ደረጃ የሚገኝ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊንም ይጨምራል፤

፮/ "ምክትል ሚኒስትር" ማለት ማንኛውም ምክትል ሚኒስትር ሲሆን በምክትል ሚኒስትር ማዕረግ የሚገኝ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊንም ይጨምራል፤

፯/ "የምክር ቤት አባል" ማለት አፈጉባዔን፣ ምክትል አፈጉባዔን እና ማንኛውንም የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባልንያጠቃልላል፤

## PART ONE
## GENERAL

### 1. Short Title

This Proclamation may be citied as the "Rights and Benefits of Outgoing Heads of State and Government, Senior Government Officials, Members of Parliament and Judges Proclamation No. 653 /2009".

### 2. Definitions

In this Proclamation, unless the context otherwise requires:

1/ "Head of State" means the President of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

2/ "Head of Government" means the Prime Minister of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the Deputy Prime Minister;

3/ "Senior Government Official" means a Minister, Minister of State or Deputy Minister;

4/ "Minister" means any Minister and includes other Senior Government Officials having the status of a Minister;

5/ "Minister of State" means any Minister of State and includes other Senior Government Officials having the status of a Minister of State;

6/ "Deputy Minister" means any Deputy Minister and includes other Senior Government Officials having the status of a Deputy Minister;

7/ "Member of Parliament" includes the Speaker, the Deputy Speaker and any member of the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

፰/ "አፈጉባዔ ወይም ምክትል አፈጉባዔ" ማለት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወይም የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈጉባዔ ወይም ምክትል አፈጉባዔ ነው፤

፱/ "የመንግሥት ተጠሪ"፣ "ምክትል የመንግሥት ተጠሪ" ወይም "ረዳት የመንግሥት ተጠሪ" ማለት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ተጠሪ፣ ምክትል የመንግሥት ተጠሪ ወይም ረዳት የመንግሥት ተጠሪ ነው፤

፲/ "የተቃዋሚ ፓርቲ መሪ" ማለት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውስጥ አብላጫውን ወንበር ከያዘው ፓርቲ ቀጥሎ ብዙ መቀመጫ ያለው ፓርቲ መሪ ነው፤

፲፩/ "የተቃዋሚ ፓርቲ ተጠሪ ወይም ረዳት ተጠሪ" ማለት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውስጥ አብላጫውን ወንበር ከያዘው ፓርቲ ቀጥሎ ብዙ መቀመጫ ያለው የተቃዋሚ ፓርቲ ተጠሪ ወይም ረደት ተጠሪ ነው፤

፲፪/ "ዳኛ" ማለት የጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዳኛ ነው፤

፲፫/ "የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ" ማለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ ሲሆን የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንቶችን ይጨምራል፤

፲፬/ "የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኛ" ማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኛ ነው፤

፲፭/ "የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዳኛ" ማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዳኛ ነው፤

፲፮/ "ባለመብት" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰጡ መብቶችና ጥቅሞችን በማግኘት ላይ ያለ ወይም ለማግኘት ብቁ የሆነ የሀገር ወይም የመንግሥት መሪ፣ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊ፣ የምክር ቤት አባል ወይም ዳኛ ነው፤

፲፯/ "ቤተሰብ" ማለት የአንድን ባለመብት የትዳር ጓደኛና ሃያ አንድ ዓመት ያልሞላቸው ልጆቹን ያጠቃልላል፤

፲፰/ "ተተኪ" ማለት አግባብ ባለው የጡረታ ሕግ የተሰጠውን ትርጓሜ ይይዛል፤

፲፱/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል።

8/ "Speaker or Deputy Speaker" means the Speaker or Deputy Speaker of the House of Peoples' Representatives or the House of the Federation;

9/ "Representative of Government", "Deputy Representative of Government" or "Assistant Representative of Government" means the Representative of Government, Deputy Representative of Government or Assistant Representative of Government in the House of Peoples' Representatives;

10/ "Opposition Party Leader" means the leader of a party having the highest number of seats next to the party holding majority seats in the House of Peoples' Representatives;

11/ "Opposition Party Representative or Assistant Representative" means the representative or assistant representative of an opposition party having the highest number of seats next to the party holding majority seats in the House of Peoples' Representatives;

12/ "Judge" means a Supreme Court, High Court or First Instance Court Judge;

13/ "Supreme Court Judge" means a Judge of the Federal Supreme Court and includes the Presidents of the Federal High Court and First Instance Court;

14/ "High Court Judge" means a Judge of the Federal High Court;

15/ "First Instance Court Judge" means a Judge of the Federal First Instance Court;

16/ "Beneficiary" means a Head of State or Government, Senior Government Official, Member of Parliament or Judge who is enjoying or entitled to the rights and benefits under this Proclamation;

17/ "Family" includes the spouse and children of a beneficiary who have not attained the age of 21 years;

18/ "Survivor" shall have the meaning given under the relevant pension law;

19/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

## ክፍል ሁለት
## ከኃላፊነት የተነሱ የሀገርና የመንግሥት መሪዎች መብቶችና ጥቅሞች

### ፫. የግል ወጪ አበል

፩/ ከኃላፊነት የተነሳ ፕሬዚዳንት፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ወይም ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር በኃላፊነት ላይ በነበረበት ጊዜ ይከፈለው የነበረው የወር ደመወዝና አበል ከኃላፊነት ሲነሳም አይቋረጥም።

፪/ በኃላፊነት ላይ ላለ ፕሬዚዳንት፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ወይም ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር የደመወዝና አበል ማስተካከያ ሲደረግ ከኃላፊነት ለተነሳ ፕሬዚዳንት፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ወይም ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርም የግል ወጪና አበል ማስተካከያ ይደረጋል።

### ፬. የመኖሪያ ቤት አገልግሎት

ከኃላፊነት የተነሳ ፕሬዚዳንት፣ ጠቅላይ ሚኒስ ትር ወይም ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ለራሱና ለቤተሰቡ መኖሪያነት የሚያገለግል የሠራተ ኞች ደመወዝን ጨምሮ በመንግሥት ወጪ የሚተዳደር ከ፬ እስከ ፭ መኝታ ክፍሎች ያሉት መኖሪያ ቤት ይሰጠዋል።

### ፭. የሕክምና አገልግሎት

፩/ ከኃላፊነት የተነሳ ፕሬዚዳንት፣ ጠቅላይ ሚኒ ስትር ወይም ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና ቤተሰቡ በመንግሥት ወጪ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር የሕክምና አገልግሎት ያገኛሉ።

፪/ የሕክምና አገልግሎቱ እንደሁኔታው በመንግ ሥት ወይም በግል የጤና ተቋም ይሰጣል። ባለመብቱና ቤተሰቡ በአገር ውስጥ የጤና ተቋም ተኝተው ሲታከሙ ሕክምና የሚሰጠው በአንደኛ ደረጃ ማዕረግ ይሆናል።

### ፮. የግል ደህንነት ጥበቃ አገልግሎት

፩/ ከኃላፊነት የተነሳ ፕሬዚዳንት፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ወይም ምክትል ጠቅላይ ሚኒስ ትር የራሱና የቤተሰቡን የግል ደህንነት የሚጠብቁ ጠባቂዎች ይመደቡለታል።

፪/ የሚመደበው የጥበቃ ኃይል ዓይነትና መጠን ጥበቃውን በሚያካሂደው አካል ይወሰናል።

## PART TWO
## RIGHTS AND BENEFITS OF OUTGOING HEADS OF STATE AND GOVERNMENT

### 3. Allowance for Personal Expenses

1/ The monthly salary and allowances paid to a President, Prime Minister or Deputy Prime Minister shall not be discontinued upon termination of his tenure.

2/ Where adjustments are made to the salary and allowances of a serving President, Prime Minister or Deputy Prime Minister, similar adjustments shall be made to the allowance for personal expenses of an outgoing President, Prime Minister or Deputy Prime Minister.

### 4. Residential House

An outgoing President, Prime Minister or Deputy Prime Minister shall be provided with a residential house having four-to-five bedrooms the administrative costs of which, including remunerations of house keeping staff, shall be covered by the Government.

### 5. Medical Benefits

1/ An outgoing President, Prime Minister or Deputy Prime Minister and his family shall get local and overseas medical services at the expense of the Government.

2/ The medical services shall, as may be appropriate, be offered at public or private health institutions. Where the beneficiary or member of his family is admitted to a local health institution, he shall be entitled to first class inpatient services.

### 6. Security Services

1/ Security guards shall be assigned to protect an outgoing President, Prime Minister or Deputy Prime Minister and his family.

2/ The composition and size of the security force shall be determined by the body in charge of the security service.

## ፯. የፕሮቶኮል አገልግሎት

ከኃላፊነት የተነሳ ፕሬዚዳንት፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ወይም ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር፡-

፩/ የዲፕሎማቲክ ፓስፖርትና የቪ.አይ.ፒ. አገልግሎት ያገኛል፤ እና

፪/ ቀድሞ የነበረውን ኃላፊነት የሚመጥን በአገር ውስጥና በውጭ አገር ሙሉ የፕሮቶኮል አገልግሎት ያገኛል።

## ፰. የተሽከርካሪ አገልግሎት

፩/ ከኃላፊነት የተነሳ ፕሬዚዳንት፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ወይም ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ደረጃቸውን የጠበቁ ሦስት ለመጓጓዣ የሚያገለግሉ የመንግሥት ተሽከርካሪዎች ይመደቡለታል።

፪/ የተሽከርካሪው ሹፌር ደመወዝ፣ የነዳጅና የጥገና እንዲሁም ሌላ ወጪ በመንግሥት ይሸፈናል።

፫/ ለባለመብቱና ለቤተሰቡ ጥበቃ አገልግሎት የሚውሉ ተሽከርካሪዎች ጥበቃውን በሚያካሂደው አካል ይወሰናል።

## ፱. የስልክ አገልግሎት

፩/ ከኃላፊነት የተነሳ ፕሬዚዳንት፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ወይም ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ወጪው በመንግሥት የሚሸፈን ሁለት መደበኛ ስልኮች በመኖሪያ ቤት ውስጥ እና አንድ ለግሉ የሚሆን ተንቀሳቃሽ ስልክ ይኖረዋል።

፪/ ለጥበቃ አገልግሎት የሚውሉት ስልኮች ዓይነትና ብዛት ጥበቃውን በሚያካሂደው አካል ይወሰናል።

## ፲. የቢሮ አገልግሎት

፩/ ከኃላፊነት የተነሳ ፕሬዚዳንት፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ወይም ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር በተለያዩ የሕዝባዊ አገልግሎቶች ላይ ከተሠማራ መኖሪያ ቤቱ በሚገኝበት ከተማ የቢሮ አገልግሎት ይሰጠዋል።

፪/ ባለመብቱ የሚመርጣቸውና መንግሥት ደመወዛቸውን የሚከፍላቸው አንድ ፀሐፊና አንድ ባለሙያ ይኖረዋል።

## 7. Protocol Service

An outgoing President, Prime Minister or Deputy Prime Minister shall be entitled to:

1/ diplomatic passport and VIP services; and

2/ full protocol service commensurate to his former position both locally and abroad.

## 8. Transport Vehicles

1/ An outgoing President, Prime Minister or Deputy Prime Minister shall be provided by the Government with three high standard transport vehicles.

2/ The running costs of the vehicles, including driver's salary, fuel and maintenance costs, shall be covered by the Government.

3/ Vehicles required for providing security services to the beneficiary and his family shall be determined by the body in charge of the security service.

## 9. Telephone Service

1/ An outgoing President, Prime Minister or Deputy Prime Minister shall be provided, at the expense of the Government, with two fixed-line telephones at his residential house and one mobile telephone for his personal communications.

2/ The type and number of telephone lines required for providing security services shall be determined by the body in charge of the security service.

## 10. Office Service

1/ If an outgoing President, Prime Minister or Deputy Prime Minister engages in various public services, he shall be provided with a place of work in the city where his residential house is located.

2/ The beneficiary shall be entitled to choose a secretary and an expert whose salary shall be paid by the Government.

፫/ ለቢሮው የሚያስፈልጉ ኮምፒዩተር፣ ስልክ፣ ኢንተርኔት፣ ፖስታ እና የመሳሰሉ ትን መንግሥት ያሟላል፤ ወጪያቸውንም ይሸፍናል።

፬/ ባለመብቱ የተሰጠውን ቢሮ ከሕዝባዊ አገል ግሎት ውጪ ለሆኑ ሥራዎች ካዋለው አገል ግሎቱ ይቋረጣል።

፭/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፬/ ድንጋጌ እንደተጠ በቀ ሆኖ፣ ባለመብቱ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ የጀመረው ሕዝባዊ አገልግሎት እስኪ ጠናቀቅ ድረስ ቤተሰቡ ቢሮውን ከአምስት ዓመት ላልበለጠ ጊዜ መገልገል ይችላል።

## ፲፩. <u>የባለመብቱ ከዚህ ዓለም በሞት መለየት</u>

፩/ ከኃላፊነት የተነሳ ፕሬዚዳንት፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ወይም ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ፡-

ሀ/ ከዚህ ዓለም በሞት መለየቱ እንደሁኔታው በወቅቱ ፕሬዚዳንት፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ወይም ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር በመን ግሥት የመገናኛ ብዙሐን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ይነገራል፤

ለ/ በመላው አገሪቱ የአንድ ቀን ብሔራዊ የሐዘን ቀን ይታወጃል፤

ሐ/ የአገሪቱ ሰንደቅ ዓላማ በፌዴራል እና በክልል መሥሪያ ቤቶች ህንፃዎች፣ በት ምህርት ቤቶች፣ ሆስፒታሎች፣ በመከላ ከያ ቢሮዎች እና ውጭ አገር ባሉ የአገሪቱ ኤምባሲዎች ዝቅ ብሎ ይውለበለባል፤

መ/ ለአስክሬኑ ሙሉ ወታደራዊ የክብር አጀብ ይደረግለታል፤

ሠ/ የቀብር ሥነ-ሥርዓቱ ወጪ በመንግ ሥት ይሸፈናል።

፪/ ባለመብቱ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫ የተመለከተው የግል ወጪ አበል ለባለቤቱ መከፈሉ ይቀጥላል። የባለመብቱ ባለቤትም ከዚህ ዓለም በሞት ከተለየች ክፍያው ሃያ አንድ ዓመት ላልሞላቸው ልጆቹ መከፈሉ ይቀጥላል።

፫/ የባለመብቱ ከዚህ ዓለም በሞት መለየት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬፣ ፭ እና ፮ መሠረት ለቤተ ሰቡ የሚሰጡትን የመኖሪያ ቤት፣ የሕክምና እና የግል ደኅንነት ጥበቃ አገልግሎቶች አያቋርጥም።

3/ The Government shall provide the necessary office facilities such as computer, telephone, internet and postal services and bear the costs thereof.

4/ The provision of office service shall be terminated if the beneficiary uses the office for any purpose other than public service.

5/ In case of death of the beneficiary and without prejudice to the provisions of sub-article (4) of this Article, his family may use the office for not more than five years until the completion of the public services commenced by the deceased.

## 11. <u>Death of Beneficiary</u>

1/ Where an outgoing President, Prime Minister or Deputy Prime Minister dies:

a) the news of his death shall be announced to the Ethiopian people by the serving President, Prime Minister or Deputy Prime Minister, as the case may be, through government mass media;

b) there shall be declared a one-day national mourning day throughout the country;

c) the National Flag shall be flown at half-mast on to federal and regional office buildings, schools, hospitals, defense offices and on to the country's Embassies overseas;

d) the cadaver shall be accompanied by a military funeral march;

e) the government shall cover expenses of the funeral ceremony.

2/ Where a beneficiary dies, the allowance for personal expenses referred to in Article 3 of this Proclamation shall continue to be paid to his spouse. Where the spouse also dies, the allowance shall continue to be paid to his children under the age of 21 years.

3/ The death of the beneficiary shall not have the effect of terminating the residential house, medical benefits and security services provided to his family under Articles 4, 5 and 6 of this Proclamation.

፬/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች ፕሬዚዳንት፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ወይም ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር በኃላፊነት ላይ እያለ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይም በተመሳሳይ ሁኔታ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

## ክፍል ሦስት
## ከኃላፊነት የተነሱ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎች መብቶችና ጥቅሞች

### ፲፪. የጡረታ መብት

፩/ አግባብ ባለው የጡረታ ሕግ በሌላ አኳኋን የተደነገገው ቢኖርም፣ ቢያንስ አንድ ሙሉ የምርጫ ዘመን ያገለገለ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊ:-

ሀ/ ከኃላፊነት ሲነሳ ዕድሜው ሃምሳ ዓመት የሞላው ከሆነ የአገልግሎት ጡረታ አበል እስከ እድሜ ልኩ ይከፈለዋል፤

ለ/ በሕመም ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሳ የሕመም ጡረታ አበል እስከ እድሜ ልኩ ይከፈለዋል፤

ሐ/ በሥራ ላይ እያለ ከዚህ ዓለም በሞት ቢለይ ለተተኪዎቹ የጡረታ አበል ይከፈላል።

፪/ ከአንድ ሙሉ የምርጫ ዘመን ያነሰ ያገለገለ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊ:-

ሀ/ ከኃላፊነት ሲነሳ ፶ ዓመት የሞላው ከሆነ የአገልግሎት ዳረጎት ይከፈለ-ዋል፤

ለ/ በሕመም ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሳ የሕመም ዳረጎት ይከፈለዋል።

፫/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚፈጸሙ ክፍያዎች መጠን የሚወሰነው አግባብ ባላቸው የጡረታ ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ይሆናል።

፬/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች አፈጻጸም በጡረታ ፈንዱ ላይ የሚያስከትለው የፋይናንስ ተጽእኖ በፌዴራል መንግሥት ይሸፈናል።

4/ The provisions of this Article shall, *mutatis* mutandis, be applicable where a President, Prime Minister or Deputy Prime Minister dies while in service.

## PART THREE
## RIGHTS AND BENEFITS OF OUTGOING SENIOR GOVERNMENT OFFICIALS

### 12. Pension Rights

1/ Notwithstanding any provision to the contrary under the relevant pension law, if a Senior Government Official who has served for at least one election term:

a) attained the age of 50 at the time of his retirement, he shall receive retirement pension for life;

b) retires because of not fulfilling the medical condition of service, he shall receive invalidity pension for life;

c) dies while in service, his survivors shall receive pension.

2/ If a Senior Government Official who has served for less than one full election term:

a) has not attained the age of 50 at the time of his retirement, he shall receive retirement gratuity;

b) retires because of not fulfilling the medical condition of service, he shall receive invalidity gratuity.

3/ The amounts of pension and gratuity payable under this Article shall be determined in accordance with the relevant provisions of pension law.

4/ The financial impact on the pension fund resulting from the application of the provisions of this Article shall be covered by the Federal Government.

## ፲፫. የመቋቋሚያ አበል

፩/ ማንኛውም ከፍተኛ የመንግሥት ኀላፊ፡-

ሀ/ ቢያንስ አንድ የምርጫ ዘመን አገልግሎ ከኃላፊነት ከተነሳ፣ ወይም

ለ/ ከአንድ የምርጫ ዘመን ግማሽ ያላነሰ አገልግሎ በሕመም፣ በአካል ጉዳት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሌላ ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሳ፣

የመቋቋሚያ አበል ይከፈለዋል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት የሚከፈለው የመቋቋሚያ አበል ለመጀመሪያው የአንድ ዓመት አገልግሎት የሦስት ወር ደመወዝ ሆኖ ከአንድ ዓመት በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ ወር ደመወዝ እየታከለ ይታሰባል። ሆኖም ጠቅላላ የመቋቋሚያ አበል ክፍያው ከአሥራ ስምንት ወር ደመወዝ መብለጥ የለበትም።

## ፲፬. የሥራ ስንብት ክፍያ

፩/ ከኃላፊነት የተነሳ ማንኛውም ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊ የሥራ ስንብት ክፍያ ይከፈለዋል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት የሚከፈለው የሥራ ስንብት ክፍያ ለመጀመሪያው የአንድ ዓመት አገልግሎት የሦስት ወር ደመወዝ ሆኖ ከአንድ ዓመት በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የመጨረሻው ወር ደመወዝ አንድ ሦስተኛ እየታከለ የሰላል። ሆኖም የሚከፈለው ጠቅላላ የሥራ ስንብት ክፍያ ከአንድ ዓመት ደመወዝ መብለጥ የለበትም።

## ፲፭. የመኖሪያ ቤት አበል

፩/ ማንኛውም ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊ፡-

ሀ/ ቢያንስ አንድ የምርጫ ዘመን አገልግሎ ከኃላፊነት ከተነሳ፣ ወይም

ለ/ ከአንድ የምርጫ ዘመን ግማሽ ያላነሰ አገልግሎ በህመም፣ በአካል ጉዳት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሌላ ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሳ፣

የመኖሪያ ቤት አበል ይከፈለዋል።

## 13. Maintenance Allowance

1/ Any Senior Government Official shall be entitled to payment of maintenance allowance if he has been released from office:

a) after serving for not less than one election term; or

b) due to sickness, disability or any other ground caused by force majeure upon completing at least half of one election term.

2/ The amount of maintenance allowance to be paid pursuant to sub-article (1) of this Article shall be equivalent to three month's salary for the first year of service, and one month's salary shall be added for every additional year of service; provided, however, that the total amount of maintenance allowance shall not exceed 18 month's salary.

## 14. Severance Pay

1/ Any Senior Government Official who has been released from office shall be entitled to severance pay.

2/ The amount of severance pay to be paid pursuant to sub-article (1) of this Article shall be equivalent to three month's salary for the first year of service, and one third of the monthly salary shall be added for every additional year of service; provided, however, that the total amount of severance pay shall not exceed one year's salary.

## 15. Housing Allowance

1/ Any Senior Government Official shall be entitled to housing allowance if he has been released from office:

a) after serving for at least one election term; or

b) due to sickness, disability or any other ground caused by force majeure upon completing at least half of one election term.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት የሚከፈለው የመኖሪያ ቤት አበል በአንድ ጊዜ የሚከፈል ሆኖ፡-

ሀ/ ለሚኒስትር ሲሆን መነሻው የስድስት ወራት ሙሉ ክፍያ ሆኖ ከአንድ የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ ወር ክፍያ አንድ ሁለተኛ እየታከለ ይሰላል፤

ለ/ ለሚኒስትር ዴኤታ ሲሆን መነሻው የሦስት ወራት ሙሉ ክፍያ ሆኖ ከአንድ የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ ወር ክፍያ አንድ ሁለተኛ እየታከለ ይሰላል፤

ሐ/ ለምክትል ሚኒስትር ሲሆን መነሻው የሁለት ወራት ሙሉ ክፍያ ሆኖ ከአንድ የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ ወር ክፍያ አንድ ሁለተኛ እየታከለ ይሰላል፤

ሆኖም የሚሰጠው ጠቅላላ ክፍያ ከ፲፰ ወር የመኖሪያ ቤት አበል መብለጥ የለበትም ።

## ፲፮. የተሽከርካሪ አበል

፩/ ማንኛውም ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊ፡-

ሀ/ ቢያንስ አንድ የምርጫ ዘመን አገልግሎ ከኃላፊነት ከተነሳ፣ ወይም

ለ/ ከአንድ የምርጫ ዘመን ግማሽ ያላነሰ አገልግሎ በህመም፣ በአካል ጉዳት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሌላ ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሳ፣

የተሽከርካሪ አበል ይከፈለዋል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት የሚከፈለው የተሽከርካሪ አበል በአንድ ጊዜ የሚከፈል ሆኖ፡-

ሀ/ ለሚኒስትር ሲሆን መነሻው የስድስት ወራት ሙሉ ክፍያ ሆኖ ከአንድ የም ርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ ወር ክፍያ አንድ ሁለተኛ እየታከለ ይሰላል፤

2/ The housing allowance under sub-article (1) of this Article shall be paid in a lump sum and its amount shall be:

a) in the case of a Minister, six month's full payment for the initial service and an addition of half of the monthly payment for every additional year of service beyond the first election term;

b) in the case of a Minister of State, three month's full payment for the initial service and an addition of half of the monthly payment for every additional year of service beyond the first election term;

c) in the case of a Deputy Minister, two month's full payment for the initial service and an addition of half of the monthly payment for every additional year of service beyond the first election term;

provided, however, that the total payment shall not exceed 18 month's housing allowance.

## 16. Vehicle Allowance

1/ Any Senior Government Official shall be entitled to vehicle allowance if he has been released from office:

a) after serving for at least one election term; or

b) due to sickness, disability or any other ground caused by force majeure upon completing at least half of one election term.

2/ The vehicle allowance under sub-article (1) of this Article shall be paid in a lump sum and its amount shall be:

a) in the case of a Minister, six month's full payment for the initial service and an addition of half of the monthly payment for every additional year of service beyond the first election term;

ለ/ ለሚኒስትር ዴኤታ ሲሆን መነሻው የሦስት ወራት ሙሉ ክፍያ ሆኖ ከአንድ የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ ወር ክፍያ አንድ ሁለተኛ እየታከለ ይሰላል፤

ሐ/ ለምክትል ሚኒስትር ሲሆን መነሻው የሁለት ወራት ሙሉ ክፍያ ሆኖ ከአንድ የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ ወር ክፍያ አንድ ሁለተኛ እየታከለ ይሰላል፤

ሆኖም የሚሰጠው ጠቅላላ ክፍያ ከ፲፰ ወር የተሽከርካሪ አበል መብለጥ የለበትም፡፡

## ፲፯. የሕክምና አገልግሎት

፩/ ከኃላፊነት የተነሳ ሚኒስትር፦

ሀ/ ለራሱና ለቤተሰቡ በአገር ውስጥ በመንግሥት የጤና ተቋም በነፃ ወይም እንደሁኔታው በግል የጤና ተቋም በመንግሥት ወጪ የሕክምና አገልግሎት ያገኛል፤

ለ/ የሕክምና ቦርድ በሚሰጠው ማስረጃ ውጭ አገር በመንግሥት ወጪ መታከም ይችላል፡፡

፪/ ከኃላፊነት የተነሳ ሚኒስትር ለራሱና ለባለቤቱ በአገር ውስጥ የጤና ተቋም ተኝቶ ለመታከም የህክምና አገልግሎት የሚሰጠው በአንደኛ ደረጃ ማዕረግ ይሆናል፡፡

፫/ ከኃላፊነት የተነሳ ሚኒስትር ዴኤታ ለራሱና ለቤተሰቡ በአገር ውስጥ በመንግሥት የጤና ተቋም በነፃ ወይም እንደሁኔታው በግል የጤና ተቋም በመንግሥት ወጪ የሕክምና አገልግሎት ያገኛል፡፡

፬/ ከኃላፊነት የተነሳ ምክትል ሚኒስትር ለራሱና ለቤተሰቡ በአገር ውስጥ በመንግሥት የጤና ተቋም የህክመና አገልግሎት በነፃ ያገኛል፡፡

b) in the case of a Minister of State, three month's full payment for the initial service and an addition of half of the monthly payment for every additional year of service beyond the first election term;

c) in the case of a Deputy Minister, two month's full payment for the initial service and an addition of half of the monthly payment for every additional year of service beyond the first election term;

provided, however, that the total payment shall not exceed 18 month's vehicle allowance.

## 17. Medical Benefit

1/ Any Ex-Minister:

a) shall get free medical services for himself and his family in public health institutions or, where appropriate, in private health institutions at the expense of the Government;

b) may get overseas medical services at the expense of the Government when recommended by a medical board.

2/ Where an Ex-Minister and his spouse are admitted to a local health institution, they shall be entitled to first class inpatient services.

3/ Any Ex-Minister of State shall get free medical services for himself and his family in local public health institutions or, where appropriate, in private health institutions at the expense of the Government.

4/ Any Ex-Deputy Minister shall get free medical services for himself and his family in local public health institutions.

## ፲፰. የግል ደህንነት ጥበቃ አገልግሎት

፩/ ማንኛውም ሚኒስትር በኃላፊነት ላይ በነበረበት ወቅት የግል ደኅንነት ጥበቃ ይደረግለት የነበረ ከሆነ ከኃላፊነት ሲነሳም ለእሱና ለቤተሰቡ ጥበቃ ይደረግለታል።

፪/ የጥበቃ ኃይሉ ዓይነትና መጠን ጥበቃውን በሚያካሂደው አካል ይወሰናል።

## ፲፱. የአገልግሎት የምስክር ወረቀት

፩/ ከኃላፊነት የተነሳ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊ፦

ሀ/ ሁለት የምርጫ ዘመን ወይም ከዛ በላይ ያገለገለ ሲሆን አንደኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት፤

ለ/ ከአንድ የምርጫ ዘመን በላይና ከሁለት የምርጫ ዘመን በታች ያገለገለ ሲሆን ሁለተኛ ደረጃ የአገልግሎት የመስክር ወረቀት፤

ሐ/ አንድ ሙሉ የምርጫ ዘመን ያገለገለ ሲሆን ሦስተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት፤

መ/ ከግማሽ የምርጫ ዘመን በላይና ከአንድ የምርጫ ዘመን በታች ያገለገለ ሲሆን አራተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት፣

ይሰጠዋል።

፪/ ከኃላፊነት ለተነሳ ሚኒስትር ወይም ሚኒስትር ዴኤታ የሚሰጥ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት በጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ለምክትል ሚኒስትር የሚሰጥ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይፈረማል።

፫/ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ማንኛውም ከኃላፊነት የተነሳ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊ፦

ሀ/ በመንግሥት ሆስፒታሎች ለሚሰጠው የሕክምና አገልግሎት ቅድሚያ ያገኛል፤

ለ/ በሕዝባዊ ስብሰባዎች የክብር ቦታ ይሰጠዋል።

፬/ አንደኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከኃላፊነት የተነሳ ሚኒስትር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፫/ ከተመለከተው ጥቅም በተጨማሪ፦

## 18. Security Service

1/ If a Minister is provided with security protection while in service, he shall be entitled to the same service for himself and his family after he has been released from office.

2/ The composition and size of the security force shall be determined by the body in charge of the security service.

## 19. Certificate of Service

1/ An Ex-Senior Government Official shall be issued with:

a) a certificate of service of 1st rank if he has served for two or more election terms;

b) a certificate of service of 2nd rank if he has served for more than one and less than two election terms;

c) a certificate of service of 3rd rank if he has served for one full election term;

d) a certificate of service of 4th rank if he has served for more than half and less than one election term.

2/ A certificate of service to be issued to a Minister or Minister of State shall be signed by the Prime Minister, and that to be issued to a Deputy Minister shall be signed by the Deputy Prime Minister.

3/ An Ex-Senior Government Official issued with a certificate of service shall be entitled to:

a) preference in getting medical services in public hospitals;

b) a seat of honour at a place where a public ceremony is held.

4/ An Ex-Minister issued with a certificate of service of 1st rank shall, in addition to the benefit provided for under sub-article (3) of this Article, be entitled to:

ሀ/ ዲፕሎማቲክ ፓስፖርት ይሰጠዋል፤

ለ/ በአውሮፕላን ማረፊያ የቪ.አይ.ፒ አገልግሎት ያገኛል፤

ሐ/ በአየር የአገር ውስጥ በረራ ሲያደርግ የአየር ትኬቱ ዋጋ ሃምሳ በመቶ በመንግሥት ይሸፈንለታል።

፭/ የሁለተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከኃላፊነት የተነሳ ሚኒስትር ወይም አንደኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከኃላፊነት የተነሳ ሚኒስትር ዴኤታ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ከተመለከተው ጥቅም በተጨማሪ፦

ሀ) ዲኘሎማቲክ ፓስፖርት ይሰጠዋል፤

ለ) በአውሮኘላን ማረፊያ የቪ.አይ.ፒ አገልግሎት ያገኛል፤

ሐ) በአየር የአገር ውስጥ በረራ ሲያደርግ የአየር ትኬቱ ዋጋ ሃያ አምስት በመቶ በመንግሥት ይሸፈንለታል።

፮/ የሦስተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከኃላፊነት የተነሳ ሚኒስትር ወይም ሁለተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከኃላፊነት የተነሳ ሚኒስትር ዴኤታ ወይም አንደኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከኃላፊነት የተነሳ ምክትል ሚኒስትር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ከተመለከተው ጥቅም በተጨማሪ፦

ሀ) ዲኘሎማቲክ ፓስፖርት ይሰጠዋል፤

ለ) በአውሮኘላን ማረፊያ የቪ.አይ.ፒ አገልግሎት ያገኛል፤

ሐ) በአየር የአገር ውስጥ በረራ ሲያደርግ የአየር ትኬቱ ዋጋ አሥር በመቶ በመንግሥት ይሸፈንለታል።

፯/ አራተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከኃላፊነት የተነሳ ሚኒስትር ወይም ሦስተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከኃላፊነት የተነሳ ሚኒስትር ዴኤታ ወይም ሁለተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከኃላፊነት የተነሳ ምክትል ሚኒስትር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ከተመለከተው ጥቅም በተጨማሪ፦

ሀ) ዲኘሎማቲክ ፓስፖርት ይሰጠዋል፤

ለ) በአውሮኘላን ማረፊያ የቪ.አይ.ፒ አገልግሎት ያገኛል።

a) diplomatic passport;

b) VIP services at airports;

c) government funding of 50% of his air fare for his local flights.

5/ An Ex-Minister issued with a certificate of service of 2nd rank or an Ex-Minister of State issued with a certificate of service of 1st rank shall, in addition to the benefit provided for under sub-article (3) of this Article, be entitled to:

a) diplomatic passport;

b) VIP services at airports;

c) government funding of 25% of his air fare for his local flights.

6/ An Ex-Minister issued with a certificate of service of 3rd rank or an Ex-Minister of State issued with a certificate of service of 2nd rank or an Ex-Deputy Minister issued with a certificate of service of 1st rank shall, in addition to the benefit provided for under sub-article (3) of this Article, be entitled to:

a) diplomatic passport;

b) VIP services at airports;

c) government funding of 10% of his air fare for his local flights.

7/ An Ex-Minister issued with a certificate of service of 4th rank or an Ex-Minister of State issued with a certificate of service of 3rd rank or an Ex-Deputy Minister issued with a certificate of service of 2nd rank shall, in addition to the benefit provided for under sub-article (3) of this Article, be entitled to:

a) diplomatic passport;

b) VIP services at airports.

፰/ አራተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከኃላፊነት የተነሳ ሚኒስትር ዴኤታ ወይም ሦስተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከኃላፊነት የተነሳ ምክትል ሚኒስትር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ከተመለከተው ጥቅም በተጨማሪ ሰርቪስ ፓስፖርት ይሰጠዋል።

## ፳. የባለመብቱ ከዚህ ዓለም በሞት መለየት

፩/ ማንኛውም ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊ በሥራ ላይ እያለ ከዚህ ዓለም በሞት ቢለይ፦

ሀ) ከመሞቱ ጋር በተያያዘ ምክንያት ለሚመጡ ወጪዎች መሸፈኛ የሦስት ወር ደመወዝ ለቤተሰቡ ይከፈላል፤

ለ) ከኃላፊነት ቢነሳ ኖሮ ሊከፈለው ይገባ የነበረው የመቋቋሚያ አበል፣ የሥራ ስንብት ክፍያ፣ የመኖሪያ ቤት አበልና የተሽከርካሪ አበል ለቤተሰቡ ይከፈላል።

፪/ ማንኛውም ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊ ከኃላፊነት ተነስቶ ጥቅሞችን ከማግኘቱ በፊት ከዚህ ዓለም በሞት ቢለይ ሊከፈለው ይገባ የነበረው የመቋቋሚያ አበል፣ የሥራ ስንብት ክፍያ፣ የመኖሪያ ቤት አበልና የተሽከርካሪ አበል ለቤተሰቡ ይከፈላል።

፫/ ማንኛውም ሚኒስትር በሥራ ላይ እያለ ወይም ከኃላፊነት ተነስቶ ከዚህ ዓለም በሞት ቢለይ፦

ሀ) ዜና ዕረፍቱና አጭር የሕይወት ታሪኩ በመንግሥት ሚዲያ ይነገራል፤

ለ) ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣን በቀብሩ ሥነ-ሥርዓት ላይ ተገኝቶ የአበባ ጉንጉን ያስቀምጣል፤

ሐ) የቀብር ሥነ-ሥርዓቱ በቀብር አስፈ - ጻሚዎች በኩል የሚፈጸም ሆኖ ወጪው በመንግሥት ይሸፈናል።

፬/ የከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊ ከዚህ ዓለም በሞት መለየት የቤተሰቡን በዚህ አዋጅ መሠረት በአገር ውስጥ የሕክምና አገልግሎት የማግኘት መብት እንዲቋረጥ አያደርግም።

8/ An Ex-Minister of State issued with a certificate of service of 4th rank or an Ex-Deputy Minister issued with a certificate of service of 3rd rank shall, in addition to the benefit provided for under sub-article (3) of this Article, be entitled to service passport.

## 20. Death of Beneficiary

1/ If a Senior Government Official dies while in service:

a) his three month's salary shall be paid to his family to cover expenses related to his death;

b) the resettlement allowance, severance pay, housing allowance and vehicle allowance that may have been due to him had he been released from office shall be paid to his family.

2/ If an Ex-Senior Government Official dies, before he has received his benefits, the resettlement allowance, severance pay, housing allowance and vehicle allowance that have been due to him shall be paid to his family.

3/ If any Minister, while in service or after being released from office, dies:

a) the news of his death, together with his short biography, shall be disclosed through government media;

b) a Senior Government Official shall attend his funeral ceremony and lay a funeral wreath;

c) the funeral ceremony shall be conducted at the expense of the Government.

4/ The death of a Senior Government Official shall not have the effect of terminating the medical benefits offered to his family at local health institutions pursuant to this Proclamation.

## ክፍል አራት

## ከኃላፊነት የተነሱ የምክር ቤት አባላት መብቶችና ጥቅሞች

### ፳፩. የጡረታ መብት

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፪ ከኃላፊነት ስለተነሱ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎች የጡረታ መብት የተደነገገው ከኃላፊነት ለተነሱ የምክር ቤት አባላትም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብነት ባለው የጡረታ ሕግ ለ "መንግሥት ሠራተኛ" የተሰጠው ትርጓሜ ማንኛውንም የምክር ቤት አባል ይሸፍናል፡፡

### ፳፪. የመቋቋሚያ አበል

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፫ ከኃላፊነት ስለተነሱ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎች የመቋቋሚያ አበል የተደነገገው ከኃላፊነት ለተነሱ የምክር ቤት አባላትም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

### ፳፫. የሥራ ስንብት ክፍያ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፬ ከኃላፊነት ስለተነሱ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎች የሥራ ስንብት ክፍያ የተደነገገው ከኃላፊነት ለተነሱ የምክር ቤት አባላትም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ ሆኖም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፱ መሠረት ወደቀድሞ ሥራው የሚመለስ የምክር ቤት አባል የሥራ ስንብት ክፍያ አያገኝም፡፡

### ፳፬. የመኖሪያ ቤት አበል

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፭ ከኃላፊነት ስለተነሱ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎች በተለይም ከኃላፊነት ስለተነሳ ሚኒስትር የመኖሪያ ቤት አበል የተደነገገው ከኃላፊነት ለተነሳ አፈጉባዔ፣ የመንግሥት ተጠሪና የተቃዋሚ ፓርቲ መሪም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፭ ከኃላፊነት ስለተነሱ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎች በተለይም ከኃላፊነት ስለተነሳ ሚኒስትር ዴኤታ የመኖሪያ ቤት አበል የተደነገገው ከኃላፊነት ለተነሳ ምክትል አፈጉባዔ፣ ምክትል የመንግሥት ተጠሪና የተቃዋሚ ፓርቲ ተጠሪም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## PART FOUR

## RIGHTS AND BENEFITS OF EX-MEMBERS OF PARLIAMENT

### 21. Pension Rights

1/ The provisions of Article 12 of this Proclamation providing for pension rights to Ex-Senior Government Officials shall also be applicable to Ex-Members of Parliament.

2/ Without prejudice to the provisions of sub-article (1) of this Article the definition given to "public servant" under the relevant pension law shall be applicable to any Member of Parliament.

### 22. Maintenance Allowance

The provisions of Article 13 of this Proclamation providing for maintenance allowance to Ex-Senior Government Officials shall also be applicable to Ex-Members of Parliament.

### 23. Severance Pay

The provisions of Article 14 of this Proclamation providing for severance pay to Ex-Senior Government Officials shall also be applicable to Ex-Members of Parliament; provided, however, that a Member who is reinstated to his former job in accordance with Article 29 of this Proclamation shall not be entitled to severance pay.

### 24. Housing Allowance

1/ The provisions of Article 15 of this Proclamation providing for housing allowance to Ex-Senior Government Officials and specifically to an Ex-Minister shall also be applicable to an Ex-Speaker, Government Representative and Opposition Party Leader.

2/ The provisions of Article 15 of this Proclamation providing for housing allowance to Ex-Senior Government Officials and specifically to an Ex-Minister of State shall also be applicable to an Ex-Deputy Speaker, Deputy Government Representative and Opposition Party Representative.

፫/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፭ ከኃላፊነት ስለተነሱ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎች በተለይም ከኃላፊነት ስለተነሳ ምክትል ሚኒስትር የመኖሪያ ቤት አበል የተደነገገው ከኃላፊነት ለተነሳ ረዳት የመንግሥት ተጠሪና የተቃዋሚ ፓርቲ ረዳት ተጠሪም ተፈጻሚ ይሆናል::

፬/ ቢያንስ አንድ የምርጫ ዘመን ያገለገለ የቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ ወይም ሌላ የምክር ቤት አባል የምክር ቤቱ የሥራ ጊዜ ከሚጠናቀቅበት የመጨረሻ ቀን አንስቶ ለሦስት ወር ያህል የመኖሪያ ቤት አበል ይከፈለዋል::

፭/ ጀምሯቸው የነበሩ ሥራዎችን ለሚቀ-ጥለው አባል ማስረከብ ያለበት የቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ወይም ምክትል ሰብሳቢ የምክር ቤቱ የሥራ ጊዜ ከሚጠናቀቅበት የመጨረሻ ቀን አንስቶ እስከ ስድስት ወር ያህል የመኖሪያ ቤት አበል ይከፈለዋል::

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ (፫) ከተመለከቱትና ከቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ወይም ምክትል ሰብሳቢ ውጭ ሥራ ማስረከብ የሚኖርበት የምክር ቤት አባል ቢኖር በአፈ ጉባኤው ውሳኔ መሰረት የምክር ቤቱ የሥራ ጊዜ ከሚጠናቀቅበት የመጨረሻ ቀን አንስቶ ቢበዛ እስከ ስድስት ወር የመኖሪያ ቤት አበል ይከፈለዋል::

## ፳፭. የተሽከርካሪ አበል

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፮ ከኃላፊነት ስለተነሱ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎች በተለይም ከኃላፊነት ስለተነሳ ሚኒስትር የተሽከርካሪ አበል የተደነገገው ከኃላፊነት ለተነሳ አፈ-ጉባዔ፣ የመንግሥት ተጠሪ እና የተቃዋሚ ፓርቲ መሪም ተፈጻሚ ይሆናል::

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፮ ከኃላፊነት ስለተነሱ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎች በተለይም ከኃላፊነት ስለተነሳ ሚኒስትር ዴኤታ የተሽከርካሪ አበል የተደነገገው ከኃላፊነት ለተነሳ ምክትል አፈ-ጉባዔ፣ ምክትል የመንግሥት ተጠሪ እና የተቃዋሚ ፓርቲ ተጠሪም ተፈጻሚ ይሆናል::

፫/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፮ ከኃላፊነት ስለተነሱ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎች በተለይም ከኃላፊነት ስለተነሳ ምክትል ሚኒስትር የተሽከርካሪ አበል የተደነገገው ከኃላፊነት ለተነሳ የመንግሥት ረዳት ተጠሪና የተቃዋሚ ፓርቲ ረዳት ተጠሪም ተፈጻሚ ይሆናል::

3/ The provisions of Article 15 of this Proclamation providing for housing allowance to Ex-Senior Government Officials and specifically to an Ex-Deputy Minister shall also be applicable to an Ex-Assistant Government Representative and Assistant Opposition Party Representative.

4/ A Chairperson or a Deputy Chairperson of a Standing Committee or any other Member of Parliament who has served for at least one election term shall be entitled to three month's housing allowance from the last day of the term of the Parliament.

5/ A Chairperson or a Deputy Chairperson of a Standing Committee who has the responsibility of handing over already commenced activities to an incoming Member shall be entitled to six month's housing allowance from the last day of the term of the Parliament.

6/ Any Member of Parliament other than those referred to in sub-articles (1) to (3) and Chairperson and a Deputy Chairperson of a Standing Committee who has the responsibility of handover functions shall, in accordance with the decision of the Speaker, be entitled to a maximum of six month's housing allowance from the last day of the term of the Parliament.

## 25. Vehicle Allowance

1/ The provisions of Article 16 of this Proclamation providing for vehicle allowance to Ex-Senior Government Officials and specifically to an Ex-Minister shall also be applicable to an Ex-Speaker, Government Representative and Opposition Party Leader.

2/ The provisions of Article 16 of this Proclamation providing for vehicle allowance to Ex-Senior Government Officials and specifically to an Ex-Minister of State shall also be applicable to an Ex-Deputy Speaker, Deputy Government Representative and Opposition Party Representative.

3/ The provisions of Article 16 of this Proclamation providing for vehicle allowance to Ex-Senior Government Officials and specifically to an Ex-Deputy Minister shall also be applicable to an Ex-Assistant Government Representative and Assistant Opposition Party Representative.

**፳፮. የሕክምና አገልግሎት**

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፮ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ከኃላፊነት ስለተነሳ ሚኒስትር የሕክምና አገልግሎት የተደነገገው ከኃላፊነት ለተነሳ አፈጉባዔ፣ የመንግሥት ተጠሪና የተቃዋሚ ፓርቲ መሪም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፮ ንዑስ አንቀጽ (፫) ከኃላፊነት ስለተነሳ ሚኒስትር ዴኤታ የሕክምና አገልግሎት የተደነገገው ከኃላፊነት ለተነሳ ምክትል አፈጉባዔ፣ ምክትል የመንግሥት ተጠሪና የተቃዋሚ ፓርቲ ተጠሪም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

፫/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፮ ንዑስ አንቀጽ (፬) ከኃላፊነት ስለተነሳ ምክትል ሚኒስትር የሕክምና አገልግሎት የተደነገገው ከኃላፊነት ለተነሳ ረዳት የመንግሥት ተጠሪና የተቃዋሚ ፓርቲ ረዳት ተጠሪም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**፳፯. የግል ደኅንነት ጥበቃ አገልግሎት**

፩/ ማንኛውም አፈጉባዔ ወይም የመንግሥት ተጠሪ በኃላፊነት ላይ በነበረበት ወቅት የግል ደኅንነት ጥበቃ ይደረግለት የነበረ ከሆነ ከኃላፊነት ሲነሳም ለእሱና ለቤተሰቡ ጥበቃ ይደረግለታል፡፡

፪/ የጥበቃ ኃይሉ ዓይነትና መጠን ጥበቃውን በሚያካሂደው አካል ይወሰናል፡፡

**፳፰. የመጓጓዣና የጓዝ ማንሻ አበል**

፩/ ማንኛውም የምክር ቤት አባል የሥራ ዘመኑ አብቅቶ ወደ ቋሚ መኖሪያው ሲመለስ ለራሱና ለቤተሰቡ የመጓጓዣና የጓዝ ማንሻ አበል በወቅቱ የትራንስፖርት ተመን መሠረት ይከፈለዋል፡፡

፪/ ማንኛውም የምክር ቤት አባል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የመጓጓዣ አበል እንዲከፈለው የመንገድ ወይም የባቡር ትራንስፖርት መጠቀም አለበት፤ ሆኖም ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ሲያጋጥመው የአየር ትራንስፖርት መጠቀም ይችላል፡፡

፫/ ማንኛውም የምክር ቤት አባል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚከፈለው የጓዝ ማንሻ ወጪ አበል እንደሚጓጓዝበት የየብስ ትራንስፖርት ዓይነት ለአባሉ ብቻ የ፩ሺ ኪሎ ግራም፣ ከባለቤቱና ከልጆቹ ጋር ከሆነ ደግሞ የ፩ሺ፭፻ ኪሎ ግራም እና ለእያንዳንዱ ልጅ ፩፻ ኪሎ ግራም ተጨማሪ ሂሳብ ይሆናል፡፡

**26. Medical Benefits**

1/ The provisions of sub-articles (1) and (2) of Article 16 of this Proclamation providing for medical benefits to an Ex-Minister shall also be applicable to an Ex-Speaker, Government Representative and Opposition Party Leader.

2/ The provisions of sub-article (3) of Article 16 of this Proclamation providing for medical benefits to an Ex-Minister of State shall also be applicable to an Ex-Deputy Speaker, Deputy Government Representative and Opposition Party Representative.

3/ The provisions of sub-article (4) of Article 16 of this Proclamation providing for medical benefits to an Ex-Deputy Minister shall also be applicable to an Ex-Assistant Government Representative and Assistant Opposition Party Representative.

**27. Security Service**

1/ If a Speaker or Government Representative is provided with security protection while in service, he shall be entitled to the same service for himself and his family after he has been released from office.

2/ The composition and size of the security force shall be determined by the body in charge of the security service.

**28. Transport and Luggage Allowance**

1/ Any Member of Parliament shall be entitled to transport and luggage allowance for himself and his family, at the rate of the current transport tariff, when he returns to the place of his permanent residence at the end of his term.

2/ A Member of Parliament shall use road or rail transport to be entitle to transport and luggage allowance in accordance with sub-article (1) of this Article; provided, however, that he may use air transport in case of force majeure.

3/ The luggage allowance to be paid to any Member of Parliament in accordance with sub-article (1) of this Article shall, depending on the type of land transport used, cover the transport cost of 1,000 kilograms of luggage for the Member alone, and 1,500 kilograms of luggage plus 100 kilograms per a child when accompanied by his spouse and children.

፬/ የምክር ቤት አባሉ በግል መኪናው የሚጠቀም ከሆነ የመኪናው ነዳጅ ወጪ በኪሎ ሜትሩ ርቀት መሠረት በመንግሥት ይሸፈናል፡፡

## ፳፱. የሥራ ምደባ

፩/ ከመመረጡ በፊት የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም የመንግሥት የልማት ድርጅት ሠራተኛ የነበረ የምክር ቤት አባል ከኃላፊነት ሲነሳ ወደቀድሞ ሥራው ለመመለስ ከጠየቀና መንግሥት ከተስማማ ወደሥራው እንዲመለስ ወይም የቀድሞ የሥራ ቦታው ክፍት ካልሆነ በተመሳሳይ የሥራ ቦታ ላይ እንዲመደብ ይደረጋል፡፡

፪/ ከኃላፊነት የተነሳው የምክር ቤት አባል ቀድሞ በነበረበት የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም የመንግሥት የልማት ድርጅት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ሊመደብ ካልቻል በሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም የመንግሥት የልማት ድርጅት በሚገኝ ተመሳሳይ ክፍት የሥራ ቦታ ላይ ሊመደብ ይችላል፡፡

፫/ የምክር ቤት አባሉ በምክር ቤቱ ውስጥ ያገለገለበት ዘመን በተመደበበት የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም የመንግሥት የል ማት ድርጅት ውስጥ እንደተሰጠ አገልግ ሎት ይቆጠርለታል፡፡

፬/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች በሹመት የሚያዙ ቦታዎችን በሚመለከት ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

## ፴. የአገልግሎት የምስክር ወረቀት

፩/ ከኃላፊነት የተነሳ የምክር ቤት አባል፡-

ሀ) ሁለት የምርጫ ዘመን ወይም ከዛ በላይ ያገለገለ ሲሆን አንደኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት፤

ለ) ከአንድ የምርጫ ዘመን በላይና ከሁለት የምርጫ ዘመን በታች ያገለገለ ሲሆን ሁለተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት፤

ሐ) አንድ ሙሉ የምርጫ ዘመን ያገለገለ ሲሆን ሦስተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት፤

መ) ከግማሽ የምርጫ ዘመን በላይና ከአንድ የምርጫ ዘመን በታች ያገለገለ ሲሆን አራተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት፤

ይሰጠዋል፡፡

4/ If the Member of Parliament uses his own transport vehicle, the fuel cost shall be calculated on the basis of the distance of his destination and shall be covered by the Government.

## 29. Reinstatement to Former Job

1/ A Member of Parliament who is released from office and who was an employee of a government office or public enterprise prior to his election shall, upon his request and the consent of the Government, be reinstated to his former job or, if it is not vacant, to a similar vacant job.

2/ If a Member of Parliament who has been released from office could not be reinstated in accordance with sub-article (1) of this Article, he may be assigned to a similar vacant job in any other government office or public enterprise.

3/ The service rendered in Parliament by the Member shall be counted in calculating the period of service he renders in the government office or public enterprise he is reinstated.

4/ The provisions of this Article shall not be applicable to job positions to be filled by appointment.

## 30. Certificate of Service

1/ An Ex-Member of Parliament shall be issued with:

a) a certificate of service of 1st rank if he has served for two or more election terms;

b) a certificate of service of 2nd rank if he has served for more than one and less than two election terms;

c) a certificate of service of 3rd rank if he has served for one full election term;

d) a certificate of service of 4th rank if he has served for more than half and less than one election term.

፪/ ከኃላፊነት ለተነሳ አፈጉባዔ፣ የመንግሥት ተጠሪ፣ ምክትል አፈጉባዔ፣ ምክትል የመንግሥት ተጠሪ ወይም የተቃዋሚ ፓርቲ መሪ የሚሰጥ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት በሀገሪቱ ፕሬዚዳንት፣ ከኃላፊነት ለተነሳ የመንግሥት ረዳት ተጠሪ፣ የተቃዋሚ ፓርቲ ተጠሪ ወይም ረዳት ተጠሪ፣ የቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ወይም ምክትል ሰብሳቢ ወይም ሌላ የምክር ቤት አባል የሚሰጥ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት በአፈጉባዔው ይፈረማል፡፡

፫/ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከኃላፊነት የተነሳ ሚኒስትር ስለሚያገኛቸው ጥቅሞች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፱ የተደነገጉት ከኃላፊነት ለተነሳ አፈጉባዔ፣ የመንግሥት ተጠሪና የተቃዋሚ ፓርቲ መሪም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

፬/ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከኃላፊነት የተነሳ ሚኒስትር ዴኤታ ስለሚያገኛቸው ጥቅሞች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፱ የተደነገጉት ከኃላፊነት ለተነሳ ምክትል አፈጉባዔ፣ ምክትል የመንግሥት ተጠሪ እና የተቃዋሚ ፓርቲ ተጠሪም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

፭/ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከኃላፊነት የተነሳ ምክትል ሚኒስትር ስለሚያገኛቸው ጥቅሞች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፱ የተደነገጉት ከኃላፊነት ለተነሳ ረዳት የመንግሥት ተጠሪና ለተቃዋሚ ፓርቲ ረዳት ተጠሪም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

፮/ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከኃላፊነት የተነሳ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊ ስለሚያገኘው ጥቅሞች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፱ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተደነገጉት ከኃላፊነት ለተነሳ ማንኛውም የምክር ቤት አባልም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**፴፩. <u>የባለመብቱ ከዚህ ዓለም በሞት መለየት</u>**

፩/ ማንኛውም የምክር ቤት አባል በሥራ ላይ እያለ ከዚህ ዓለም በሞት ቢለይ፦

ሀ) ከመሞቱ ጋር በተያያዘ ምክንያት ለሚመጡ ወጪዎች መሸፈኛ የሦስት ወር ደመወዝ ለቤተሰቡ ይከፈላል፤

ለ) ከኃላፊነት ቢነሳ ኖሮ ሊከፈለው ይገባ የነበረው የመቋቋሚያ አበል፣ የሥራ ስንብት ክፍያ፣ የመኖሪያ ቤት አበልና የተሽከርካሪ አበል ለቤተሰቡ ይከፈላል፡፡

2/ A certificate of service to be issued to an Ex-Speaker, Government Representative, Deputy Speaker, Deputy Government Representative or Opposition Party Leader shall be signed by the President of the Country, and that to be issued to an Ex-Assistant Government Representative, Opposition Party Representative or Assistant Representative, Chairperson or Deputy Chairperson of a Standing Committee or any other Member of Parliament shall be signed by the Speaker.

3/ The provisions of Article 19 of this Proclamation providing for benefits to an Ex-Minister issued with a certificate of service shall also be applicable to an Ex-Speaker, Government Representative and Opposition Party Leader.

4/ The provisions of Article 19 of this Proclamation providing for benefits to an Ex-Minister of State issued with a certificate of service shall also be applicable to an Ex-Deputy Speaker, Deputy Government Representative and Opposition Party Representative.

5/ The provisions of Article 19 of this Proclamation providing for benefits to an Ex-Deputy Minister issued with a certificate of service shall also be applicable to an Ex-Assistant Government Representative and Assistant Opposition Party Representative.

6/ The provisions of sub-article (3) of Article 19 of this Proclamation providing for benefits to an Ex-Senior Official issued with a certificate of service shall also be applicable to an Ex-Member of Parliament.

**31. <u>Death of Beneficiary</u>**

1/ If a Member of Parliament dies while in service:

a) his three month's salary shall be paid to his family to cover expenses related to his death;

b) the resettlement allowance, severance pay, housing allowance and vehicle allowance that may have been due to him had he been released from office shall be paid to his family.

፪/ ማንኛውም የምክር ቤት አባል ከኃላፊነት ተነስቶ ጥቅሞችን ከማግኘቱ በፊት ከዚህ ዓለም በሞት ቢለይ ሊከፈለው ይገባ የነበረው የመቋቋሚያ አበል፣ የሥራ ስንብት ክፍያ፣ የመኖሪያ ቤት አበልና የተሽከርካሪ አበል ለቤተሰቡ ይከፈላል፡፡

፫/ አፈጉባዔ፣ የመንግሥት ተጠሪ ወይም የተቃዋሚ ፓርቲ መሪ በሥራ ላይ እያለ ወይም ከኃላፊነት ተነስቶ ከዚህ ዓለም በሞት ቢለይ፡-

ሀ) ዜና ዕረፍቱና አጭር የሕይወት ታሪኩ በመንግሥት ሚዲያ ይነገራል፤

ለ) ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣን በቀብሩ ሥነ-ሥርዓት ላይ ተገኝቶ የአበባ ጉንጉን ያስቀምጣል፤

ሐ) የቀብር ሥነ-ሥርዓቱ በቀብር አስፈ-ጻሚዎች በኩል የሚፈጸም ሆኖ ወጪው በመንግሥት ይሸፈናል፡፡

፬/ የአፈጉባዔ፣ የመንግሥት ተጠሪ፣ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪ፣ የምክትል አፈጉባዔ፣ የምክትል የመንግሥት ተጠሪ፣ የተቃዋሚ ፓርቲ ተጠሪ፣ ረዳት የመንግሥት ተጠሪ ወይም የተቃዋሚ ፓርቲ ረዳት ተጠሪ ከዚህ ዓለም በሞት መለየት የቤተሰቡን በዚህ አዋጅ መሠረት በአገር ውስጥ የሕክምና አገልግሎት የማግኘት መብት እንዲቋረጥ አያደርግም፡፡

## ክፍል አምስት

## ከኃላፊነት የተነሱ ዳኞች መብቶችና ጥቅሞች

### ንዑስ ክፍል አንድ

### ከኃላፊነት የተነሳ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ወይም ምክትል ፕሬዚዳንት መብቶችና ጥቅሞች

**፴፪. ጠቅላላ**

የዚህ ንዑስ ክፍል ድንጋጌዎች በጡረታ ምክንያት ከኃላፊነት ለተነሱ የፌዴራል የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

**፴፫. የግል ወጪ አበል**

፩/ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ወይም ምክትል ፕሬዚዳንት በኃላፊነት ላይ በነበረበት ጊዜ ይከፈለው የነበረው የወር ደመወዝ ከኃላፊነት ሲነሳም አይቋረጥም፡፡

2/ If an Ex-Member of Parliament dies, before he has received his benefits, the resettlement allowance, severance pay, housing allowance and vehicle allowance that have been due to him shall be paid to his family.

3/ If a Speaker, Government Representative or an Opposition Party Leader, while in service or after being released from office, dies:

a) the news of his death, together with his short biography, shall be announced through government media;

b) a Senior Government Official shall attend his funeral ceremony and lay a funeral wreath;

c) the funeral ceremony shall be conducted at the expense of the Government.

4/ The death of a Speaker, Government Representative, Opposition Party Leader, Deputy Speaker, Deputy Government Representative, Opposition Party Representative, Assistant Government Representative or Assistant Opposition Party Representative shall not have the effect of terminating the medical benefits offered to his family at local health institutions pursuant to this Proclamation.

## PART FIVE

## RIGHTS AND BENEFITS OF EX-JUDGES

### SECTION ONE

### RIGHTS AND BENEFITS OF OUTGOING PRESIDENT AND DEPUTY PRESIDENT OF THE SUPREME COURT

**32. General**

The provisions of this Section shall be applicable to outgoing President and Deputy President of the Federal Supreme Court released from office due to retirement.

**33. Allowance for Personal Expenses**

1/ The monthly salary and allowances paid to a President or Deputy President of the Supreme Court shall not be discontinued upon his release from office.

፪/ በኃላፊነት ላይ ላለ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ኘሬዚዳንት ወይም ምክትል ፕሬዚዳንት የደመወዝ ማስተካከያ ሲደረግ ከኃላፊነት ለተነሳ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ኘሬዚዳንት ወይም ምክትል ፕሬዚዳንትም የግል ወጪና አበል ማስተካከያ ይደረጋል፡፡

## ፴፬. የመኖሪያ ቤት አገልግሎት

ከኃላፊነት የተነሳ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ወይም ምክትል ፕሬዚዳንት ለራሱና ለቤተሰቡ መኖሪያነት የሚያገለግል በመንግሥት ወጪ የሚተዳደር ከ፫ እስከ ፬ መኝታ ክፍሎች ያሉት መኖሪያ ቤት ይሰጠዋል፡፡

## ፴፭. የሕክምና አገልግሎት

፩/ ከኃላፊነት የተነሳ የጠቅላይ ፍረድ ቤት ፕሬዚዳንት ወይም ምክትል ፕሬዚዳንት እና ቤተሰቡ በመንግሥት ወጪ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር የሕክምና አገልግሎት ያገኛሉ፡፡

፪/ የሕክምና አገልግሎቱ እንደሁኔታው በመንግሥት ወይም በግል የጤና ተቋም ይሰጣል፡፡ ባለመብቱ እና ቤተሰቡ በአገር ውስጥ የጤና ተቋም ተኝተው ሲታከሙ ሕክምና የሚሰጠው በአንደኛ ደረጃ ማዕረግ ይሆናል፡፡

## ፴፮. የግል ደህንነት ጥበቃ አገልግሎት

፩/ ከኃላፊነት የተነሳ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ወይም ምክትል ፕሬዚዳንት የራሱና የቤተሰቡን የግል ደህንነት የሚጠብቁ ጠባቂዎች ይመደቡለታል፡፡

፪/ የሚመደበው የጥበቃ ኃይል ዓይነትና መጠን ጥበቃውን በሚያካሂደው አካል ይወሰናል፡፡

## ፴፯. የኘሮቶኮል አገልግሎት

ከኃላፊነት የተነሳ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ወይም ምክትል ፕሬዚዳንት፣

፩/ የዲኘሎማቲክ ፓስፖርትና የቪ.አይ.ፒ አገልግሎት ያገኛል፤ እና

፪/ ቀድሞ የነበረውን ኃላፊነት የሚመጥን በአገር ውስጥና በውጭ አገር ሙሉ የኘሮቶኮል አገልግሎት ያገኛል፡፡

2/ Where adjustments are made to the salary and allowances of a serving President or Deputy President of the Supreme Court, similar adjustments shall be made to the allowance for personal expenses of an outgoing President or Deputy President of the Supreme Court.

## 34. Residential House

An outgoing President or Deputy President of the Supreme Court shall be provided with a residential house having three-to-four bedrooms the administrative costs of which shall be covered by the Government.

## 35. Medical Benefits

1/ An outgoing President or Deputy President of the Supreme Court and his family shall get local and overseas medical services at the expense of the Government.

2/ The medical services shall, as may be appropriate, be offered at public or private health institutions. Where the beneficiary or member of his family is admitted to a local health institution, he shall be entitled to first class inpatient services.

## 36. Security Service

1/ Security guards shall be assigned to protect an outgoing President or Deputy President of the Supreme Court and his family.

2/ The composition and size of the security force shall be determined by the body in charge of the security service.

## 37. Protocol Service

An outgoing President or Deputy President of the Supreme Court shall be entitled to:

1/ diplomatic passport and VIP services; and

2/ full protocol service commensurate to his former position both locally and abroad.

**፴፰. <u>የተሽከርካሪ አገልግሎት</u>**

፩/ ከኃላፊነት የተነሳ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ወይም ምክትል ፕሬዚዳንት ደረጃቸውን የጠበቁ ሁለት ለመጓጓዣ የሚያገለግሉ የመንግሥት ተሽከርካሪዎች ይመደቡለታል፡፡

፪/ የተሽከርካሪው ሹፌር ደመወዝ፣ የነዳጅና የጥገና እንዲሁም ሌላ ወጪ በመንግሥት ይሸፈናል፡፡

፫/ ለባለመብቱና ለቤተሰቡ ጥበቃ አገልግሎት የሚውሉ ተሽከርካሪዎች ጥበቃውን በሚያካሂደው አካል ይወሰናል፡፡

**፴፱. <u>የስልክ አገልግሎት</u>**

፩/ ከኃላፊነት የተነሳ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ወይም ምክትል ፕሬዚዳንት ወጪው በመንግሥት የሚሸፈን ሁለት መደበኛ ስልኮች በመኖሪያ ቤት ውስጥ እና አንድ ለግሉ የሚሆን ተንቀሳቃሽ ስልክ ይኖረዋል፡፡

፪/ ለጥበቃ አገልግሎት የሚውሉት ስልኮች ዓይነትና ብዛት ጥበቃውን በሚያካሂደው አካል ይወሰናል፡፡

**፵. <u>የቢሮ አገልግሎት</u>**

፩/ ከኃላፊነት የተነሳ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ወይም ምክትል ፕሬዚዳንት በተለያዩ የሕዝባዊ አገልግሎቶች ላይ ከተሠማራ መኖሪያ ቤቱ በሚገኝበት ከተማ የቢሮ አገልግሎት ይሰጠዋል፡፡

፪/ ባለመብቱ የሚመርጣቸውና መንግሥት ደመወዛቸውን የሚከፍላቸው አንድ ፀሐፊና አንድ ባለሙያ ይኖረዋል፡፡

፫/ ለቢሮው የሚያስፈልጉ ኮምፒዩተር፣ ስልክ፣ ኢንተርኔት፣ ፖስታ እና የመሳሰሉትን መንግሥት ያሟላል፤ ወጪያቸውንም ይሸፍናል፡፡

፬/ ባለመብቱ የተሰጠውን ቢሮ ከሕዝባዊ አገልግሎት ውጪ ለሆነ ሥራ ካዋለው አገልግሎቱ ይቋረጣል፡፡

፭/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ባለመብቱ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ የጀመረው ሕዝባዊ አገልግሎት እስኪጠናቀቅ ድረስ ቤተሰቡ ቢሮውን ከአምስት ዓመት ላልበለጠ ጊዜ መገልገል ይችላል፡፡

**38. <u>Transport Vehicles</u>**

1/ An outgoing President or Deputy President of the Supreme Court shall be provided by the Government with two high standard transport vehicles.

2/ The running costs of the vehicles, including driver's salary, fuel and maintenance costs, shall be covered by the Government.

3/ Vehicles required for providing security services to the beneficiary and his family shall be determined by the body in charge of the security service.

**39. <u>Telephone Service</u>**

1/ An outgoing President or Deputy President of the Supreme Court shall be provided, at the expense of the Government, with two fixed-line telephones at his residential house and one mobile telephone for his personal communications.

2/ The type and number of telephone lines required for providing security services shall be determined by the body in charge of the security service.

**40. <u>Office Service</u>**

1/ If an outgoing President or Deputy President of the Supreme Court engages in various public services, he shall be provided with a place of work in the city where his residential house is located.

2/ The beneficiary shall be entitled to choose a secretary and an expert whose salary shall be paid by the Government.

3/ The Government shall provide the necessary office facilities such as computer, telephone, internet and postal services and bear the costs thereof.

4/ The provision of office service shall be terminated if the beneficiary uses the office for any purpose other than public service.

5/ In case of death of the beneficiary and without prejudice to the provisions of sub-article (4) of this Article, his family may use the office for not more than five years until the completion of the public services commenced by the deceased.

## ፵፩. <u>የባለመብቱ ከዚህ ዓለም በሞት መለየት</u>

፩/ ከኃላፊነት የተነሳ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ወይም ምክትል ፕሬዚዳንት ከዚህ ዓለም በሞት ቢለይ፡-

ሀ) ዜና ዕረፍቱ እና አጭር የሕይወት ታሪኩ በመንግሥት ሚዲያ ይነገራል፤

ለ) ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣን በቀብሩ ሥነ-ሥርዓት ላይ ተገኝቶ የአበባ ጉንጉን ያስቀምጣል፤

ሐ) የቀብር ሥነ-ሥርዓቱ በቀብር አስፈጻሚዎች በኩል የሚፈጸም ሆኖ ወጪው በመንግሥት ይሸፈናል።

፪/ ባለመብቱ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፫ የተመለከተው የግል ወጪ አበል ለባለቤቱ መከፈሉ ይቀጥላል። የባለመብቱ ባለቤትም ከዚህ ዓለም በሞት ከተለየች ክፍያው ሃያ አንድ ዓመት ላልሞላቸው ልጆቹ መከፈሉ ይቀጥላል።

፫/ የባለመብቱ ከዚህ ዓለም በሞት መለየት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፬፣ ፴፭ እና ፴፮ መሠረት ለቤተሰቡ የሚሰጡትን የመኖሪያ ቤት፣ የሕክምና እና የግል ደኅንነት ጥበቃ አገልግሎቶች አያቋርጥም።

፬/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ወይም ምክትል ፕሬዚዳንት በኃላፊነት ላይ እያለ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይም በተመሳሳይ ሁኔታ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

### <u>ንዑስ ክፍል ሁለት</u>
### <u>ከኃላፊነት የተነሱ ዳኞች መብቶችና ጥቅሞች</u>

## ፵፪. <u>ጠቅላላ</u>

የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፬ (፩)(ለ)፣ ፵፮ (፩)(ለ)፣ ፵፯ (፩)(ለ) እና ፶፩ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፣ የዚህ ንዑስ ክፍል ድንጋጌዎች የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንትን ሳይጨምር በጡረታ ምክንያት ከኃላፊነት ለተነሱ ለሌሎች ዳኞች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

## ፵፫. <u>የጡረታ መብት</u>

ከኃላፊነት የተነሱ ዳኞች ጡረታ የሚያገኙት አግባብ ባለው የጡረታ ሕግ መሠረት ይሆናል።

## 41. <u>Death of Beneficiary</u>

1/ Where an outgoing President or Deputy President of the Supreme Court dies:

a) the news of his death, together with his short biography, shall be disclosed through government media;

b) a Senior Government Official shall attend his funeral ceremony and lay a funeral wreath;

c) the funeral ceremony shall be conducted at the expense of the Government.

2/ Where a beneficiary dies, the allowance for personal expenses referred to in Article 33 of this Proclamation shall continue to be paid to his spouse. Where the spouse also dies, the allowance shall continue to be paid to his children under the age of 21 years.

3/ The death of the beneficiary shall not have the effect of terminating the residential house, medical benefits and security services provided to his family under Articles 34, 35 and 36 of this Proclamation.

4/ The provisions of this Article shall, *mutatis mutandis*, be applicable where a President or Deputy President of the Supreme Court dies while in service.

### <u>SECTION TWO</u>
### <u>RIGHTS AND BENEFITS OF EX-JUDGES</u>

## 42. <u>General</u>

Without prejudice to the provisions of Articles 44(1)(b), 46(1)(b), 47(1)(b) and 51 of this Proclamation, the provisions of this Section shall be applicable to Judges, other than the President and Deputy President of the Supreme Court, released from office due to retirement.

## 43. <u>Pension Rights</u>

Ex-Judges shall be entitle to pension rights in accordance with the relevant pension law.

## ፵፬. የመቋቋሚያ አበል

፩/ ማንኛውም ዳኛ:-

ሀ) ቢያንስ አምስት ዓመት አገልግሎ ከኃላፊነት ከተነሳ፣ ወይም

ለ) ከሁለት ዓመት ተኩል ያላነሰ አገልግሎ በህመም፣ በአካል ጉዳት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሌላ ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሳ፣

የመቋቋሚያ አበል ይከፈለዋል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚከፈለው የመቋቋሚያ አበል ለመጀመሪያው የአንድ ዓመት አገልግሎት የሦስት ወር ደመወዝ ሆኖ ከአንድ ዓመት በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ ወር ደመወዝ እየታከለ ይታሰባል፡፡ ሆኖም ጠቅላላ የመቋቋሚያ አበል ክፍያው ከአሥራ ስምንት ወር ደመወዝ መብለጥ የለበትም፡፡

## ፵፭. የሥራ ስንብት ክፍያ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፬ ከኃላፊነት ስለተነሱ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎች የሥራ ስንብት ክፍያ የተደነገገው ከኃላፊነት ለተነሱ ዳኞችም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ፵፮ የመኖሪያ ቤት አበል

፩/ ማንኛውም ዳኛ፡-

ሀ) ቢያንስ አምስት ዓመት አገልግሎ ከኃላፊነት ከተነሳ፣ ወይም

ለ) ከሁለት ዓመት ተኩል ያላነሰ አገል ግሎ በህመም፣ በአካል ጉዳት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሌላ ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሳ፣

የመኖሪያ ቤት አበል ይከፈለዋል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚከፈለው የመኖሪያ ቤት አበል በአንድ ጊዜ የሚከፈል ሆኖ፣

ሀ) ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ ሲሆን መነሻው የስድስት ወራት ሙሉ ክፍያ ሆኖ ከአምስት ዓመት በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ ወር ክፍያ አንድ ሁለተኛ እየታከለ ይሰላል፤

## 44. Maintenance Allowance

1/ Any Judge shall be entitled to payment of maintenance allowance if he has been released from office:

a) after serving for not less than five years; or

b) due to sickness, disability or any other ground caused by force majeure after serving at least two and half years.

2/ The amount of maintenance allowance to be paid pursuant to sub-article (1) of this Article shall be equivalent to three month's salary for the first year of service, and one month's salary shall be added for every additional year of service; provided, however, that the total amount of maintenance allowance shall not exceed 18 month's salary.

## 45. Severance Pay

The provisions of Article 14 of this Proclamation providing for severance pay to Ex-Senior Government Officials shall also be applicable to Ex-Judges.

## 46. Housing Allowance

1/ Any Judge shall be entitled to payment of housing allowance if he has been released from office:

a) after serving for not less than five years; or

b) due to sickness, disability or any other ground caused by force majeure after serving at least two and half years.

2/ The housing allowance under sub-article (1) of this Article shall be paid in a lump sum and its amount shall be:

a) in the case of a Supreme Court Judge, six month's full payment for the initial service and an addition of half of the monthly payment for every additional year of service beyond five years of service;

ለ) ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኛ ሲሆን መነሻው የሦስት ወራት ሙሉ ክፍያ ሆኖ ከአምስት ዓመት በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ ወር ክፍያ አንድ ሁለተኛ እየታከለ ይሰላል፤

ሐ) ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዳኛ ሲሆን መነሻው የሁለት ወራት ሙሉ ክፍያ ሆኖ ከአምስት ዓመት በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ ወር ክፍያ አንድ ሁለተኛ እየታከለ ይሰላል፤

ሆኖም የሚሰጠው ጠቅላላ ክፍያ ከ፲፰ ወር የመኖሪያ ቤት አበል መብለጥ የለበትም።

## ፵፯. የተሽከርካሪ አበል

፩/ ማንኛውም ዳኛ፡-

ሀ) ቢያንስ አምስት ዓመት አገልግሎ ከኃላፊነት ከተነሳ፣ ወይም

ለ) ከሁለት ዓመት ተኩል ያላነሰ አግልግሎ በህመም፣ በአካል ጉዳት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሌላ ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሳ፣

የተሽከርካሪ አበል ይከፈለዋል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚከፈለው የተሽከርካሪ አበል በአንድ ጊዜ የሚከፈል ሆኖ፣

ሀ) ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ ሲሆን መነሻው የስድስት ወራት ሙሉ ክፍያ ሆኖ ከአምስት ዓመት በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ ወር ክፍያ አንድ ሁለተኛ እየታከለ ይሰላል፤

ለ) ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኛ ሲሆን መነሻው የሦስት ወራት ሙሉ ክፍያ ሆኖ ከአምስት ዓመት በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ ወር ክፍያ አንድ ሁለተኛ እየታከለ ይሰላል፤

ሐ) ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዳኛ ሲሆን መነሻው የሁለት ወራት ሙሉ ክፍያ ሆኖ ከአምስት ዓመት በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ ወር ክፍያ አንድ ሁለተኛ እየታከለ ይሰላል፤

ሆኖም የሚሰጠው ጠቅላላ ክፍያ ከ፲፰ ወር የተሽከርካሪ አበል መብለጥ የለበትም።

b) in the case of a High Court Judge, three month's full payment for the initial service and an addition of half of the monthly payment for every additional year of service beyond five years of service;

c) in the case of a First Instance Court Judge, two month's full payment for the initial service and an addition of half of the monthly payment for every additional year of service beyond five years of service ;

provided, however, that the total payment shall not exceed 18 month's housing allowance.

## 47. Vehicle Allowance

1/ Any Judge shall be entitled to payment of vehicle allowance if he has been released from office:

a) after serving for not less than five years; or

b) due to sickness, disability or any other ground caused by force majeure after serving at least two and half years.

2/ The vehicle allowance under sub-article (1) of this Article shall be paid in a lump sum and its amount shall be:

a) in the case of a Supreme Court Judge, six month's full payment for the initial service and an addition of half of the monthly payment for every additional year of service beyond five years of service;

b) in the case of a High Court Judge, three month's full payment for the initial service and an addition of half of the monthly payment for every additional year of service beyond five years of service;

c) in the case of a First Instance Court Judge, two month's full payment for the initial service and an addition of half of the monthly payment for every additional year of service beyond five years of service ;

provided, however, that the total payment shall not exceed 18 month's vehicle allowance.

## ፵፰. የሕክምና አገልግሎት

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፯ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ከኃላፊነት ስለተነሳ ሚኒስትር የሕክምና አገልግሎት የተደነገገው ከኃላፊነት ለተነሳ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፯ ንዑስ አንቀጽ (፫) ከኃላፊነት ስለተነሳ ሚኒስትር ዴኤታ የሕክምና አገልግሎት የተደነገገው ከኃላፊነት ለተነሳ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኛም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

፫/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፯ ንዑስ አንቀጽ (፬) ከኃላፊነት ስለተነሳ ምክትል ሚኒስትር የሕክምና አገልግሎት የተደነገገው ከኃላፊነት ለተነሳ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዳኛም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 48. Medical Benefits

1/ The provisions of sub-articles (1) and (2) of Article 17 of this Proclamation providing for medical benefits to an Ex-Minister shall also be applicable to an Ex-Supreme Court Judge.

2/ The provisions of sub-article (3) of Article 17 of this Proclamation providing for medical benefits to an Ex-Minister of State shall also be applicable to an Ex-High Court Judge.

3/ The provisions of sub-article (4) of Article 17 of this Proclamation providing for medical benefits to an Ex-Deputy Minister shall also be applicable to an Ex-First Instance Court Judge.

## ፵፱. የግል ደህንነት ጥበቃ አገልግሎት

፩/ ማንኛውም የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ በኃላፊነት ላይ በነበረበት ወቅት የግል ደኅንነት ጥበቃ ይደረግለት የነበረ ከሆነ ከኃላፊነት ሲነሳም ለእሱና ለቤተሰቡ ጥበቃ ይደረግለታል፡፡

፪/ የጥበቃ ኃይሉ ዓይነትና መጠን ጥበቃውን በሚያካሂደው አካል ይወሰናል፡፡

## 49. Security Service

1/ If a Supreme Court Judge is provided with security protection while in service, he shall be entitled to the same service for himself and his family after he has been released from office.

2/ The composition and size of the security force shall be determined by the body in charge of the security service.

## ፶. የአገልግሎት የምስክር ወረቀት

፩/ ከኃላፊነት የተነሳ ዳኛ፡-

ሀ) ከ፲፭ ዓመት በላይ ያገለገለ ሲሆን አንደኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት፤

ለ) ከ፲ ዓመት በላይ እስከ ፲፭ ዓመት ያገለገለ ሲሆን ሁለተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት፤

ሐ) ከአምስት ዓመት በላይ እስከ ፲ ዓመት ያገለገለ ሲሆን ሦስተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት፤

መ) ከሁለት ዓመት ተኩል እስከ አምስት ዓመት ያገለገለ ሲሆን አራተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት፣

ይሰጠዋል፡፡

፪/ ከኃላፊነት ለተነሳ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ የሚሰጥ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት በጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ከኃላፊነት ለተነሳ የከፍተኛ ወይም የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዳኛ የሚሰጥ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት በጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ይፈረማል፡፡

## 50. Certificate of Service

1/ An Ex-Judge shall be issued with:

a) a certificate of service of 1st rank if he has served for more than 15 years;

b) a certificate of service of 2nd rank if he has served for more than 10 up to 15 years;

c) a certificate of service of 3rd rank if he has served for more than 5 up to 10 years;

d) a certificate of service of 4th rank if he has served for more than two and half years up to five years.

2/ A certificate of service to be issued to an Ex-Supreme Court Judge shall be signed by the Prime Minister, and that to be issued to an Ex-High Court or First Instance Court Judge shall be signed by the President of the Supreme Court.

፫/ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከኃላፊነት የተነሳ ሚኒስትር ስለሚያገኛ ቸው ጥቅሞች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፱ የተደነገገው ከኃላፊነት ለተነሳ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

፬/ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከኃላፊነት የተነሳ ሚኒስትር ዴኤታ ስለሚያገኛቸው ጥቅሞች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፱ የተደነገገው ከኃላፊነት ለተነሳ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኛም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

፭/ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከኃላፊነት የተነሳ ምክትል ሚኒስትር ስለሚያገኛቸው ጥቅሞች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፱ የተደነገገው ከኃላፊነት ለተነሳ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዳኛም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ፶፩. <u>የባለመብቱ ከዚህ ዓለም በሞት መለየት</u>

፩/ ማንኛውም ዳኛ በሥራ ላይ እያለ ከዚህ ዓለም በሞት ቢለይ፡-

ሀ) ከመሞቱ ጋር በተያያዘ ምክንያት ለሚመጡ ወጪዎች መሸፈኛ የሦስት ወር ደመወዝ ለቤተሰቡ ይከፈላል፤

ለ) ከኃላፊነት ቢነሳ ኖሮ ሊከፈለው ይገባ የነበረው የመቋቋሚያ አበል፣ የሥራ ስንብት ክፍያ፣ የመኖሪያ ቤት አበልና የተሽከርካሪ አበል ለቤተሰቡ ይከፈላል፡፡

፪/ ማንኛውም ዳኛ ከኃላፊነት ተነስቶ ጥቅሞችን ከማግኘቱ በፊት ከዚህ ዓለም በሞት ቢለይ ከኃላፊነት ቢነሳ ኖሮ ሊከፈለው ይገባ የነበረው የመቋቋሚያ አበል፣ የሥራ ስንብት ክፍያ፣ የመኖሪያ ቤት አበልና የተሽከርካሪ አበል ለቤተሰቡ ይከፈላል፡፡

፫/ ማንኛውም የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ በሥራ ላይ እያለ ወይም ከኃላፊነት ተነስቶ ከዚህ ዓለም በሞት ቢለይ፡-

ሀ) ዜና ዕረፍቱና አጭር የሕይወት ታሪኩ በመንግሥት ሚዲያ ይነገራል፤

ለ) ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣን በቀብሩ ሥነ-ሥርዓት ላይ ተገኝቶ የአበባ ጉንጉን ያስቀምጣል፤

ሐ) የቀብር ሥነ-ሥርዓቱ በቀብር አስፈጻ-ሚዎች በኩል የሚፈጸም ሆኖ ወጪው በመንግሥት ይሸፈናል፡፡

3/ The provisions of Article 19 of this Proclamation providing for benefits to an Ex-Minister issued with a certificate of service shall also be applicable to an Ex-Supreme Court Judge.

4/ The provisions of Article 19 of this Proclamation providing for benefits to an Ex-Minister of State issued with a certificate of service shall also be applicable to an Ex-High Court Judge.

5/ The provisions of Article 19 of this Proclamation providing for benefits to an Ex-Deputy Minister issued with a certificate of service shall also be applicable to an Ex-First Instance Court Judge.

## 51. <u>Death of Beneficiary</u>

1/ If a Judge dies while in service:

a) his three month's salary shall be paid to his family to cover expenses related to his death;

b) the resettlement allowance, severance pay, housing allowance and vehicle allowance that may have been due to him had he been released from office shall be paid to his family.

2/ If an Ex-Judge dies, before he has received his benefits, the resettlement allowance, severance pay, housing allowance and vehicle allowance that have been due to him shall be paid to his family.

3/ If a Supreme Court Judge, while in service or after being released from office, dies:

a) the news of his death, together with his short biography, shall be disclosed through government media;

b) a Senior Government Official shall attend his funeral ceremony and lay a funeral wreath;

c) the funeral ceremony shall be conducted at the expense of the Government.

፬/ የማንኛውም ዳኛ ከዚህ ዓለም በሞት መለየት የቤተሰቡን በዚህ አዋጅ መሠረት በአገር ውስጥ የሕክምና አገልግሎት የማግኘት መብት እንዲቋረጥ አያደርግም::

## ክፍል ስድስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፶፪. የመኖሪያ ቤትና የተሽከርካሪ አበል ተመን

፩/ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከፈል የመኖሪያ ቤት አበል ተመን የየወቅቱን የመኖሪያ ቤት ኪራይ መጠን ግምት ውስጥ በማስገባት የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል::

፪/ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከፈል የተሽከርካሪ አበል ተመን የየወቅቱን የነዳጅ፣ የቅባት፣ የዘይት፣ የጥገናና ተሽከርካሪ ለማንቀሳቀስ የሚያስፈልጉ ሌሎች ወጪዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል::

### ፶፫. የአገልግሎት ዘመን አቆጣጠርና የመብቶች ግንኙነት

፩/ ማንኛውም ከኃላፊነት የተነሳ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊ ከመሾሙ በፊት በምክር ቤት አባልነት የሰጠው አገልግሎት በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚያዝ አገልግሎት ይታሰብለታል::

፪/ ማንኛውም ከኃላፊነት የተነሳ የምክር ቤት አባል ከመመረጡ በፊት በከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊነት የሰጠው አገልግሎት በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚያዝ አገልግሎት ይታሰብለታል::

፫/ ከኃላፊነት የተነሳ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊ ወይም የምክር ቤት አባል ከመሾሙ ወይም ከመመረጡ በፊት በክልል መንግሥት ከፍተኛ ኃላፊነት ወይም በክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባዔነት ወይም ምክትል አፈ-ጉባዔነት ወይም ሙሉ ጊዜውን በቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢነት የሰጠው አገልግሎት በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚያዝ አገልግሎት ይታሰብለታል::

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)፣ (፪) ወይም (፫) የተጠቀሰው የቀድሞ አገልግሎት በዚህ አዋጅ ወይም በሚመለከተው ክልል ሕግ መሠረት ለባለመብቱ አስቀድሞ መብትና ጥቅም ያስገኘለት ከሆነ በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚያዝ አገልግሎት አይታሰብም::

4/ The death of a Judge shall not have the effect of terminating the medical benefits offered to his family at local health institutions pursuant to this Proclamation.

## PART SIX
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 52. Rate of Housing and Vehicle Allowances

1/ The rate of housing allowance to be paid pursuant to this Proclamation shall be determined by directives of the Council of Ministers issued in consideration of the current rates of house rent.

2/ The rate of vehicle allowance to be paid pursuant to this Proclamation shall be determined by directives of the Council of Ministers issued in consideration of the current costs of fuel, grease, oil, maintenance and other running costs of vehicles.

### 53. Computation of Service and Relations of Benefits

1/ The service of any Ex-Senior Government Official rendered as a Member of Parliament prior to his appointment shall be considered in computing his service pursuant to this Proclamation.

2/ The service of any Ex-Member of Parliament rendered as a Senior Government Official prior to his election shall be considered in computing his service pursuant to this Proclamation.

3/ The service of any Ex-Senior Government Official or Ex-Member of Parliament rendered as a State Government Senior Official, Speaker or Deputy Speaker of State Council or fulltime Chairperson of a Standing Committee of State Council prior to his appointment or election shall be considered in computing his service pursuant to this Proclamation.

4/ Any previous service referred to in sub-article (1), (2) or (3) of this Article shall not be considered in computing service pursuant to this Proclamation if the beneficiary has already acquired rights and benefits relating to the said service in accordance with this Proclamation or the legislation of the concerned State.

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)፣ (፪) ወይም (፫) የተጠቀሰው የቀድሞ አገልግሎት የተሻለ መብትና ጥቅም የሚያስገኝ ከሆነ ባለመብቱ ይህንኑ የተሻለውን መብትና ጥቅም እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

፮/ በአንድ ጊዜ የምክር ቤት አባልና ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊ የነበረ ባለመብት በምክር ቤት አባልነቱና በከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊነቱ ከሚያገኛቸው መብቶችና ጥቅሞች የሚበልጠውን ያገኛል፡፡

፯/ ከኃላፊነት የተነሳ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊ በተለያዩ የኃላፊነት ደረጃዎች ላይ ተመድቦ አገልግሎት የሰጠ ከነበረ በማናቸውም ጊዜ ተመድቦበት ለነበረው ከፍተኛው የኃላፊነት ደረጃ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰጠው መብትና ጥቅም ይጠበቅለታል፡፡

## ፶፬. <u>መብቶችንና ጥቅሞችን የሚያሳጡ ሁኔታዎች</u>

፩/ ማንኛውም የሀገር ወይም የመንግሥት መሪ ወይም ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊ፡-

ሀ) የመንግሥት ፖሊሲዎችን ባለመፈጸሙ ወይም ባለማስፈጸሙ፤

ለ) በሥልጣኑ ያለአግባብ በመጠቀሙ፤

ሐ) የሙስና ተግባር በመፈጸሙ፤

መ) ሚስጥራዊ መረጃዎችን ላልተፈቀደለት ወገን በመግለጹ ወይም አሳልፎ በመስጠቱ፣ ወይም

ሠ) በወንጀል ወይም በዲስፕሊን የሚያስጠይቅ ማናቸውንም ሌላ ድርጊት በመፈጸሙ፤

ምክንያት ከኃላፊነት እንዲወገድ የተደረገ ከሆነ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰጡትን መብቶችና ጥቅሞች አያገኝም፡፡

፪/ ማንኛውም የምክር ቤት አባል፡-

ሀ) የመራጮችን አመኔታ በማጣቱ፣ ወይም

ለ) በሥነምግባር ብልሹነት፣

ምክንያት ከአባልነት እንዲወገድ የተደረገ ከሆነ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰጡትን መብቶችና ጥቅሞች አያገኝም፡፡

5/ Where the previous service referred to in sub-article (1), (2) or (3) of this Article entitles the beneficiary with better rights and benefits, such rights and benefits shall be applicable.

6/ Where a beneficiary was a Member of Parliament and Senior Government Official at the same time, he shall be entitled to the rights and benefits of an Ex-Member of Parliament or Ex-Senior Government Official, which ever is higher.

7/ Where an Ex-Senior Government Official has served at different levels of a Senior Government Official's position, he shall be entitled to the rights and benefits applicable, in accordance with this Proclamation, to the highest position he assumed at any time of his tenure.

## 54. <u>Deprivation of Rights and Benefits</u>

1/ Any Head of State or Government or Senior Government Official shall not be entitled to the rights and benefits under this Proclamation if he is removed from office on the ground that he has:

a) failed to implement or cause the implementation of government policies;

b) abused his power;

c) involved in corrupt practices;

d) given or disclosed confidential informations to a party not entitled to;

e) committed any other offence entailing criminal or disciplinary liabilities.

2/ Any Member of Parliament shall not be entitled to the rights and benefits under this Proclamation if he has lost his mandate:

a) for having no confidence of the electorate; or

b) due to misconduct.

፫/ ተገቢውን ሥርዓት ሳይከተል ከኃላፊነቱ የለቀቀ የሀገር ወይም የመንግሥት መሪ ወይም ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊ ወይም የምክር ቤት አባል በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰጡትን መብቶችና ጥቅሞች አያገኝም፡፡

## ፶፭. መብቶችንና ጥቅሞችን የሚያቋርጡ ሁኔታዎች

፩/ በዚህ አዋጅ መሠረት የተገኙ መብቶችና ጥቅሞች በሚከተሉት ምክንያቶች ይቋረጣሉ፡-

ሀ) ማንኛውም ባለመብት፤

(፩) ህገ መንግሥታዊ ሥርዓትን ለማፍረስ ከሞከረ፤

(፪) የሀገርን ሉአላዊነት አደጋ ላይ በሚጥል ተግባር ከተሳተፈ፤

(፫) የሀገር ክህደት ወንጀል ከፈጸመ፤

(፬) በኃላፊነት ላይ በነበረ ጊዜ ያገኛ ቸውን ሀገራዊ ጉዳዮች የሚመለከቱ ሚስጥራዊ መረጃዎች ካልጠበቀ፤ ወይም

(፭) ህገ መንግሥቱንና በህገመንግሥቱ መሠረት የተቋቋሙትን ተቋማት ካላከበረ፤

ለ) ከኃላፊነት የተነሳ ፕሬዚዳንት የአንድ ፖለቲካ ፓርቲ ወይም ድርጅት አባል ከሆነ፤

ሐ) ከኃላፊነት የተነሳ የሀገር ወይም የመንግሥት መሪ ወይም የጠቅላይ ፍርድ ቤት ኘሬዚዳንት ወይም ምክትል ፕሬዚዳንት ይዞት ከነበረው ኃላፊነት ጋር በሚቃረን ወይም ክብሩን በሚያጎድፍ ሥራ ላይ ከተቀጠረ ወይም በእንዲህ ዓይነቱ ማንኛውም ሥራ ላይ በመሠማራት ገቢ ካገኘ፤

መ) ከኃላፊነት የተነሳ ዳኛ በጥብቅና ሥራ ላይ የተሠማራ ከሆነ፤

ሠ) ከኃላፊነት የተነሳ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊ ሲመራው ከነበረው የመንግሥት መሥሪያ ቤት ጋር ቀጥታ ግንኙነት ባለው የግል ድርጅት ወይም በየነመንግሥታዊ ባልሆነ ዓለም አቀፍ ድርጅት ወይም መንግሥታዊ ባልሆነ ድርጅት ከኃላፊነት ከተነሳበት ጊዜ ጀምሮ ሁለት ዓመት ሳይሞላው ከተቀጠረ፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩(ሀ) መሠረት መብቶችና ጥቅሞች የሚቋረጡት ባለመብቱ ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት የጥፋተኛነት ውሳኔ ከተሰጠበት በኋላ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ ሲወሰን ይሆናል፡፡

3/ Any Head of State or Government or Senior Government Official or Member of Parliament shall not be entitled to the rights and benefits under this Proclamation if he has resigned without following the prescribed procedure.

## 55. Termination of Rights and Benefits

1/ The enjoyment of rights and benefits under this Proclamation shall be terminated where:

a) any beneficiary:

(1) attempts to disrupt the constitutional order;

(2) involves in any act endangering the sovereignty of the country;

(3) commits an act of treason;

(4) fails to keep the confidentiality of secureable informations related to the affairs of the nation known to him during his office responsibility;

(5) fails to respect the Constitution and bodies constituted under the Constitution;

b) an Ex-President becomes a member of a political party or organization;

c) an outgoing Head of State or Government or an outgoing President or Deputy President of the Supreme Court is employed on a job or earns income from any activity, which is conflicting with his former position or incompatible with his status;

d) an Ex-Judge engages in rendering advocacy services;

e) an Ex-Senior Government Official is employed, within two years from the date of his release, by any private organization or international organization other than intergovernmental organization or by non-governmental organization, that has direct relationship with the government office he was in charge of.

2/ The termination of rights and benefits pursuant to sub-article (1)(a) of this Article shall be effected upon the decision of the House of Peoples' Representatives following the conviction of the beneficiary by the competent court.

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)(ለ)፣ (ሐ)፣ (መ) ወይም (ሠ) መሠረት መብቶችና ጥቅሞች የሚቋረጡት ባለመብቱ ጥፋተኛ መሆኑ በፌዴራል ስነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከተጣራ በኋላ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ ሲወሰን ይሆናል፡፡

፬/ ከኃላፊነት የተነሳ የሀገር ወይም የመንግሥት መሪ ወይም የጠቅላይ ፍርድ ቤት ኘሬዚዳንት ወይም ምክትል ፕሬዚዳንት በቅጥር ወይም ገቢ በሚያስገኝ ሌላ ሥራ ላይ ከመሠማራቱ በፊት ከደረጃው ጋር አብሮ የማይሄድ ስለአለመሆኑ ከፌዴራል ስነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን የተሰጠ ማረጋገጫ ማግኘት አለበት፡፡

፭/ በዚህ አዋጅ መሠረት በተሠጠው መብት ወይም ጥቅም ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል መጠቀም የማይፈልግ ባለመብት ይህንኑ ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ አለበት፡፡

3/ The termination of rights and benefits pursuant to sub-article (3)(b), (c), (d) or (e) of this Article shall be effected upon the decision of the House of Peoples Representatives following the investigation, conducted by the Federal Ethics and Anti-Corruption Commission, on the offense committed by the beneficiary.

4/ An outgoing Head of State or Government or President or Deputy President of the Supreme Court shall, before engaging in an employment or any other income generating activity, obtain a clearance from the Federal Ethics and Anti-Corruption Commission.

5/ A beneficiary shall notify the appropriate body the total or partial waiver of his rights and benefits under this Proclamation if he wishes so.

## ፶፮. ለአዲስ ተሿሚዎች የሚደረግ የገንዘብ ድጋፍ

፩/ አዲስ የተሾመ ወይም የተመረጠ ሚኒስትር፣ አፈጉባዔ፣ የመንግሥት ተጠሪ፣ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪ፣ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት፣ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት ወይም የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ ለመቋቋሚያ ይረዳው ዘንድ የማይመለስ የሁለት ወር ደመወዝ ይሰጠዋል፡፡

፪/ አዲስ የተሾመ ወይም የተመረጠ ሚኒስትር ዴኤታ፣ ምክትል ሚኒስትር፣ ምክትል አፈጉባዔ፣ ምክትል ወይም ረዳት የመንግሥት ተጠሪ ወይም የተቃዋሚ ፓርቲ ተጠሪ ወይም ረዳት ተጠሪ ለመቋቋሚያ ይረዳው ዘንድ የማይመለስ የአንድ ወር ደመወዝ ይሰጠዋል፡፡

## 56. Financial Support upon New Appointment

1/ A newly appointed or elected Minister, Speaker, Government Representative, Opposition Party Leader, President of the Supreme Court, Deputy President of the Supreme Court or a Supreme Court Judge shall be granted non-repayable two month's salary to facilitate his settlement.

2/ A newly appointed or elected Minister of State, Deputy Minister, Deputy Speaker, Deputy or Assistant Government Representative, Opposition Party Representative or Assistant Representative shall be granted non-repayable one month's salary to facilitate his settlement.

## ፶፯. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችንና መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 57. Power to Issue Regulations and Directives

The Council of Ministers may issue regulations and directives necessary for the implementation of this Proclamation.

## ፶፰. የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

፩/ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት መተዳደሪያ አዋጅ ቁጥር ፪፻፶፭/፲፱፻፺፬ በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

፪/ ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## 58. Repealed and Inapplicable Laws

1/ The Administration of the President of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 255/2001 is hereby repealed.

2/ No law, regulation, directive or practice shall, in so far as it is inconsistent with this Proclamation, have force or effect in respect of matters provided for in this Proclamation.

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ በአዋጅ ቁጥር ፪፻፶፭/፲፱፻፺፬ መሠረት የተገኙና ይህ አዋጅ እስከጸናበት ጊዜ ድረስ ጸንተው የቆዩ መብቶችንና ጥቅሞችን አያስቀርም፡፡

3/ The provisions of sub-article (1) of this Article shall not affect rights and benefits acquired under Proclamation No. 255/2001 and remained valid until the effective date of this Proclamation.

## ፶፱. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከሐምሌ ፩ ቀን ፪ሺ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

## 59. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall enter into force as of the 8th day of July, 2008.

**አዲስ አበባ ጳጉሜ ፬ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**Done at Addis Ababa, this 9th day of September, 2009**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**